# ፍቅርና ሰላም

በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች የሚታተም ወርሃዊ ጋዜጣ

A Monthly Amharic/English Newspaper Published by the Catholic Bishop's Conference of Ethiopa (CBCE)

General Secretariat/ECS

# LINK

ቁጥር 567 | ሐምሌ 2016 ዓ.ም | ዋጋው የኢ.ት. 15.00 ብር


01 ወር ቀረው

ካቶሊካዊ ሲኖዶስ 2014 2016

ለሲኖዶሳዊት ቤተ ክርስቲያን ኅብረት / ተሳትፎ / ተልእኮ

## የቅዱስ ጴጥሮስ መንበር ርዕሰ ጉብኝት "አድ ሊሚና"



ሰኞ ሰኔ 17 ቀን 2016 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ብፁዓን ጳጳሳት በሕብረት የቅዱስ ጴጥሮስ መንበር ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ በአካል መገናኘት ወይም በላቲን ቋንቋ 'አድ ሊሚና'። ይህ ሥርዓት በመላው ዓለም የሚገኙ ካቶሊካውያን ጳጳሳት ጉባኤዎች በየአምስት ዓመቱ አንድ ጊዜ የሚያደርጉት የቤተክርስቲያን ጉብኝት ነው።

ገፅ 5

## ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነየሱስ ሊቀጳጳሳት ዘካቶሊካውያን የ2016 ዓ.ም. የፍልሰታ ፆም መግቢያን አስመልክተው ያስተላለፉት መልእክት

ገፅ 3

## ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ ክቡር አባ ጌታሁን ፋንታን አዲሱ የነቀምት ሀገረ ስብከት ጳጳስ ብለው መሰየማቸውን ቫቲካን ሐምሌ 9 ቀን 2016 ዓ.ም. አወጀ



## የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ሊቀጳጳስ ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነየሱስ ሐምሌ 14 ቀን 2016 ዓ.ም በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ ዞን በመሬት መንሸራተት ምክንያት በተከሰተው አደጋ እጅግ ማዘናቸውን ገለፁ

ገፅ 4

## የክቡር አባ ኃይሌ ሚካኤል (ደጀኔ) ሂዶቶ የሲመተ ጵጵስና ሥርዓት መስከረም 5 ቀን 2016 ዓ.ም. በሶዶ ቅድስት ሥላሴ ካቶሊክ ካቴድራል እንደሚካሄድ ተገለጸ

ገፅ 10

## የቅዱስ ዮሐንስ ጳውሎስ ሁለገብ ማዕከል በይፋ ተመረቀ

ገፅ 1



## በኢትዮጵያ የአገልግሎት ጊዜያቸውን የፈጸሙ የቅድሰት መንበር እንደራሴ ምስጋና አቀረቡ

ገፅ 5

## የአዲግራት ሀገረስብከት የሰበካ ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች ጉብኘት

ገፅ 8

የብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነየሱስ የ25ተኛ የጵጵስና የብሩራዊ ኢዮቤልዩ ዓመትን በማስመልከት ሥጦታ ለማቅረብ ለሚፈልጉ ሁሉ የቁሳዊ ሥጦታ ቀርቶ የትምህርት ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወጣቶች እንደሚውል በማሰብ ካርዲናል አቡነ ብርሃነየሱስ የሚል የገንዘብ ድጋፍ ዕድል መመቻቸቱን ገልጸው በተዘጋጀው የባንክ አካውንት መላው ካቶሊካውያን እና በጎ ፍቃድ ያላቸው ሁሉ ለዚህ በጎ አድራጎት ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

**Cardinal Berhaneyesus Fund**

Account Name: **Cardinal Berhaneyesus Fund**
Account Number: **1000523294338**
Commercial Bank of Ethiopia, Mahatema Gandhi Branch
Swift Code: **CBETETAA**

ፍቅርና ሰላም
መስከረም 1967 ዓ. ም. ተጀመረ
አሳታሚ ቤተ ሊቀ ጳጳሳት ዘካቶሊካውያን

በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት የማኅበራዊ መገናኛና ሕዝብ ግንኙነት ማስተባበሪያ በየወሩ ተዘጋጅቶ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ዋና አዘጋጅ | አባ አበራ ማኬቦ
ምክትል ዋና አዘጋጅ | አቤል ሙሴ
ማኔጂንግ ኤዲተር | ቤዛዊት አሰፋ
ተቀዳሚ ረዳት አዘጋጅና ሪፖርተር/ኤዲተር | ገብሩ ሃ/ዮሐንስ
ምክትል ረዳት አዘጋጅ | መሳይ ማሪዮ
ፕሩፍ ሪደር | የምሥራች አሰፋ
ሌይ አውት 1 | ጨረታ ዘውዴ
ሌይ አውት 2 | ቤተልሔም ታደሰ
ስርጭት | ማኅበራዊ መገናኛና ሕዝብ ግንኙነት ማስተባበሪያ

ፖ. ሣ. ቁ. 2454 አዲስ አበባ ስልክ - (0111) 55 03 00 ፋክስ (0111) 55 31 13 E-Mail - scpr@eccsdco.org Website - https//www.cbce-gs.org

# ርዕሰ አንቀጽ

# ወላዲተ አምላክ ለአዳም ዘር ሁሉ የፍቅር እናት

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለማርያም የሚያበሥራት ከሁሉም የሚበልጠውን ታላቅ ዜና ይኸውም የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ ሆኖ የሚመጣበት የደህንነት የምሥራቹ መልዕክት ዛሬም ሕያው ነው።

*በፀጋ የተሞላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ*
*እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነው። (ሉቃ.1፡-28 )*

እግዚአብሔር የሰው ሥጋ ለብሶ ሰው ሲሆን ሰማይና ምድር በድጋሚ መዋሀድ ነው። ማርያም እግዚአብሔር በማህፀኗ ለመቀበል ሙሉ በሙሉ ፈቅዳለችና። መልሷም "እነሆ የጌታ ባርያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ"( ሉቃ. 1፡ - 38) ነበር። ለዚህ ነው ወላዲተ አምላው የያዕቆብ መሰላል የምንላት ምክንያቱም በሰማይና በምድር መካከል አገናኝ በመሆንዋ ነው። እንደዚሁም የመንግሥተ ሰማይ በር ተብላ ትጠራለች ምክንቱያም እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ መልክ ወደ ሰዎች መካከል የሚገባው በእርሷ አማካይነት ነውና።

እግዚአብሔር ሁልጊዜ የእኛን ነፃ ምላሽ ይጠብቃል እንጂ የማንንም ሰው አእምሮ ከቶ አያስገድድም። እያንዳንዳችን የእግዚአብሔርን ፍቅር ለመመለስ ሙሉ ነፃነት አለን። አባታችን ሆይ "ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነ እንዲሁም በምድር ይሁን" በምንልበት ጊዜ ማርያም በፈፀመችው መንገድ እኛም ለእግዚአብሔር ምላሽ መስጠታችን አንዘንጋ። በፀሎታችን ማብቂያ "አሜን" በምንልበት ጊዜ "ይሁን" የሚለውን ምላሽ ለእግዚአብሔር መስጠታችን ነው። ማርያም ይሁን ባለችበት ቅጽበት ቅዱስ ገብርኤል ያመጣው መልእክት ተፈጸመ። እርሱ ከዘመናት በፊት ከአብ ተወለደ፤ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ወደ ምድር መጣ፤ በመፈስ ቅዱስ ተፀነሰ፤ ከድንግል ማርያም ሥጋ ለብሶ ሰው ሆነ (ቀኖና ሃይማኖት)። የመልአኩ መልዕክት ከኢሳያስ ትንቢት ጋር ፍጹም ተመሳሰለ።

ሕያው አምላክ የሆነውን ክርስቶስ ወደ እግዚአብሔር አብ ሊመልሰንና ከእርሱ ጋር ሊያስታርቀን ይፈልጋል። የጠፋውንን ምስላችንን እንደገና የሚመልሰልንም እርሱ ነው። የእግዚአብሔር አምሳልነታችንን መልሰን እንድናገኝ ዘንድ ራሱን በእኛ መሰለ። "ሰው አምላክ እንዲሆን አምላክ ሰው ሆነ" ከአምላክ ጋር ይህን ውህደት ሙሉ በሙሉ መጀመሪያ የፈፀመችና በዚህ መንገድም ዛሬ ኮከብ ሆና የምትመራን ማርያም ነች።

## የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ታዛዥነት

ታዛዥነት ከእግዚአብሔር የጸጋ ሙላት የሚመነጭ የትሕትና ፍሬ ነው። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ደግሞ ትሑት ስለሆነች ታዛዥ ነበረች። የሔዋንየእንቢተኝነት ቋጠሮ በማርያም ተፈታ፤ ሔዋን ባለማመንዋ ያሰረችውን ነገር እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በማመንዋ ፈታችው። ብፅዕት ቅድስት ድንግል ማርያም ስላመነችና ስለታዘዘች፣ የእግዚአብሔርን ልጅ በምድር ላይ ወለደችው። ለመውለድ የበቃችው ከወንድ ሳትገናኝ ከመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው። ቅዱሳን አበው በሔዋንና በማርያም መካከል ንጽጽር በማድረግ ለማርያም "የሔዋን እናት" ብለው ይጠሩዋታል፤ ቀጥሎም "ሞት በሔዋን መጣ" "ሕይወት ግን በማርያም መጣ" ይላሉ። ቅዱሳን በእመቤታችን ማርያም ታዛዥነትና፣ ስለ ታዛዥነትን ጥቅም እንዲህ እያሉ ይናገራሉ። ቅዱስ አጎስጢኖስ "ያቺ የመለኮታዊው እናት በመታዘዟ፣ ሔዋን ባለመታዘዟ ያመጣችብንን ጉዳት ካሠች" ይላል። ቅዱስ ቤርናርዶስ፣ "ሰማች - አየች፤ ሰማች - አመነች፤ አየች - ገባት ጆሮዎቿን ለመታዘዝ አዘነበለች" ይላል። "በብፅዕት ድንግል ማርያም፣ መዘግየት የሚባል ነገር የለም። ስለዚህ ልክ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚንቀሳቀስ ተሽከርካሪ ነበረች" ይላል።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ደግሞ እንደ ልጇ፣ ከልጅነት እስከ ሞት ታዛዥ ሆነች። ይህንን ከባድ የታዛዥነት ቀንበር በደስታ ተሸከመችው። ለማን ትታዘዝ ነበር? መጀመርያ ለእግዚአብሔር ፣ በመቀጠል ለሰው ትታዘዝ ነበር።

## የወላዲተ አምላክ ዕረፍትና ፍልሰታ

በቅዱሳት መጽሐፍት ስለ ወላዲተ አምላክ ዕረፍትና ፍልሰታ ባይጻፍም ቤተክርስቲያን በተሰጣት መለኮታዊ ፀጋና ስልጣን በጥር 21 አስተርዮዋን እና ነሐሴ 16 ትንሣኤዋ ሲዘከር ይኖራል። ማርያም ከሞት ወደ ሕይወት መሸጋገሯን ፍርድ ሳትቀበል የዘላለም ሕይወት መጎናፀፍዋን ወንጌላዊ ዮሐንስ፤ "እውነት እውነት እላችኋለሁ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም (ዮሐ. 5፡- 24)። እኛም በዚህ ቃልና እምነት የሕይወት እናት በመበስበስ አትሸነፍም የምንለው።

ቅዱሳን አበው በዝማሬያቸው መቃብርም ሆነ ሞት ወላዲተ አምላክን ይዞ ማስቀረት አይቻለውም፣ እርስዋ የሕይወት እናት ናትና፣ በጸሎት የተጋች ናት፣ በአማላጅነቷ ተስፋችን የጸና ነው። በድንግል ማኅፀኗ ባደረው በክርስቶስ ወደ ሕይወት ተለወጠች በማለት ያመሰግኗታል።

**ሃሌ ሉያ! መላእክት ወደ ሰማይ ወሰዱአት**

እርስዋ አንደበትዋ ጣፋጭ ሥራዋም
ድንቅ ነው
እርስዋ የነቢያትና የሐዋርያት ወዳጅ ናት
እርስዋ የጻድቃንና የሰማዕታት ወዳጅ ናት
በዚያ ለሰው ዘር ሁሉ ተጸልያለች
በማለት ወላዲተ አምላክ ሆይ ሰላም
ላንቺ ይሁን፣ ልጅሽ ወደ ሕይወት ወደ
እግዚአብሔር መንግሥት ጠራሽ በማለት
ዛሬም ምስጋና ማቅረባችን አንተው፡

## ያለ አዳም ኃጢአት የተፀነሰች

ወላዲተ አምላክ እንደ ማንኛውም ሰው ከአንድ አባትና እናት ተፀንሳ የተወለደች ብትሆንም ቤተክርስቲያናችን የእርስዋን ጽንሰት ከሌሎች በዓይነቱና በይዘቱ ለየት ያለ እንደሆነ ታምናለች፣ ታስተምራለችም። በአንድ ጊዜ ፈጣሪዋና ልጅዋ እንደሆነው እንደ ክርስቶስ መፀነስ ዓይነት የእርስዋም ከአዳምና ሔዋን ኃጢአት ወይም ከጥንት አብሶ ነፃ የሆነ ነው። ይሁን እንጂ ይህን እውነት አንዳንድ የቤተክርስቲያን አባቶች ከጥንት ጊዜ ጀምረው ያስተማሩት ቢሆንም ቤተ ክርስቲያን እንደ እምነት ድንጋጌ አድርጋ ለማወጅ ብዙ ዘመናትን ፈጅቶባታል። ያወጀችውም እ.ኤ.አ. በ1854 ዓ.ም ነው።

የሁለተኛ የቫቲካን ጉባኤ አባቶችም (እ.ኤ.አ. 1964 - 65 ዓ.ም) "ወላዲተ አምላክ በደኅንነት መንገድ ያላት ተሳትፎ፣ ቦታና ክብርዋ የዓለም አዳኝ ከሆነው ልጅዋ ከክርስቶስ የማይነጣጠል በቀጥታም ከዚያ አንድነት የሚመነጭ ነው ብለዋል። ስለዚህ የማርያም ጥሪዋና ተልዕኮዋ በድንገት ወይም በዕድል የሆነ ሳይሆን በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ ውስጥ የነበረ ነው። እግዚአብሔር ከታላቅ ምሕረቱና ደግነቱ የተነሣ በኃጢአት ባልቆሸሹ በአዲሱ አዳም በክርስቶስ በአዲሲቱ ሔዋን በማርያም በኩል ድኅንነትን ለሰው ልጆች ለመስጠት ፈቀደ።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በሐሳቧ፣ በአነጋገሯ፣ በሥራዋ፣ ታዛዥነቷ ለራሷ ምንም ሳታስቀር ለእግዚአብሔር በሁለንተናዋ አስገዛች። በመታዘዟ ምክንያት እግዚአብሔር ክብርን አጎናፀፋት።

ዛሬ ላይ እኛስ እንደ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የእግዚአብሔርን ቅዱስ ፈቃድ ከልባችን በታዛዥነት መንፈስ ቶሎ ብለን እንፈጽመዋለን ወይ? እስኪ እነዚህንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ሕሊናችንን ሰንመረምር ለወላጆቻችን፣ ለቤተ ክርስቲያን ኃላፊዎች፣ ለመሪዎቻችን፣ እንዴት አድርገን ነው የምንታዘዘው? በጥላቻ፣ በንቀት ወይ በቸልተኝነትና በማጉረምረም ነው የምንታዘዘው? የእግዚአብሔር ድምጽ የሆነችው ሕሊናችን ምን ትለን ይሆን? ዘወትር የመታዘዝ እና የትሕትና ተምሳሌት የሆነችው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በአማላጅነትዋ *"ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ"( ዮሐ.2፡-5)* የምትለንን ቃል ለመስማትና ለመታዘዝ ያብቃን።

*ነፍሴ ሆይ ኃጢአትን እንጂ ሞትን አትፍሪ (ምህላ ዘዘመነ ፍልሰታ)*

## የዕርቀ ሰላም ጸሎት

ፈጣሪ ሆይ የሰላም መሳሪያ እንድንሆን
አድርገን።
ጥላቻ ባለበት ፍቅር፤ በደል ባለበት ይቅርታ፤
ክርክር ባለበት ስምምነት፤ ጥርጣሬ ባለበት
መተማመን፤ ሐዘን ባለበት ደስታ፤ ጨለማ
ባለበት ብርሃን፤ እንዲገኝ እናደርግ ዘንድ
አብቃን።
ፈጣሪ ሆይ፤ በሕዝባችን መካከል ዕርቅ
ይውረድ፤ ሰላምህ ይስፈን፤ አገራችን ኢትዮጵያን
ባርክልን ጠብቅልን።
አሜን!

## የሲኖዶሳዊ ጉዞ ጸሎት

**መንፈስ ቅዱስ ሆይ! ና!**

**እነሆ በስምህ ተሰብስበን በፊትህ ቆመናል ወደ እኛ ተመልከት፤ እርዳንም። ብቸኛ መሪያችን አንተ ነህ ልቦቻችንን ከፍተህ ማደርያህ አድርግልን። ማድረግ ያለብንን ሁሉ አንተ አስተምረን፣ ሁላችንም በአንድ ላይ መከተል ያለብንን መንገድ አንተ አሳየን። እኛ ደካሞች እና ኃጢአተኞች ነንና፤ ሁከት እንዳናስፋፋ፣ አላዋቂነት ወደ ተሳሳተ ጎዳና እንዳይመራን፣ አድልዎ በድርጊቶቻችን ላይ ተጽዕኖ እንዳያሳድርብን እርዳን። ከእውነት መንገድ እንዳንስት፣ ወደ ዘለዓለማዊ እና ትክክል ወደሆነው ሕይወት አብረን እንጓዝ ዘንድ ከአንተ ብቻ የሆነውን የሕብረት መንፈስን ስጠን።**

**ይህን ሁሉ በሁሉም ቦታ እና በሁሉም ሰዓት ከአብ እና ከወልድ ጋር አብረህ በሥራ ላይ የምትኖርን አንተን እንለምንሃለን፤ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም አሜን።**

**"ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ"( ዮሐ.2፡-5)**

# ብፁዕ አቡነ ካርዲናል ብርሃነየሱስ ሊቀጳጳሳት ዘካቶሊካውያን የ2016 ዓ.ም. የፍልሰታ ፆም መግቢያን አስመልክተው ያስተላለፉት መልእክት

*በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!*

***‹‹ታላቅ ምልክትም በሰማይ ታየ ፀሐይን ተጐናጽፋ ጨረቃ ከእግሮችዋ በታች ያላት በራስዋም ላይ የአሥራ ሁለት ከዋክብት አክሊል የሆነላት አንዲት ሴት ነበረች። እርስዋም ፀንሳ ነበር...አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች››። ራዕ. 12፡ 1-2፤5)***

የተወደዳችሁ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች፡ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔር ፍቅርና የመንፈስ ቅዱስ አንድነት ከሁላችሁ ጋር በማለት የከበረ ሰላምታዬን አቀርብላችኋለሁ። የዘንድሮ ዓመት የፍልሰታን ጾም በምንጾምበት ጊዜ ሁሌም ስንጾም እንደምናደርገው ሁሉ በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መቆየት የተቸገሩትን በምንችለው አቅም መርዳትና የታመሙትንና የታሰሩትን መጎብኘት የጾመችን ዋናው ተግባራት ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ እናታችን ንጽሕት ድንግል ማርያም «ከአዳም ኃጢአት ሁሉ ተጠብቃ የምድራዊ ሕይወቷ ጉዞ ሲያበቃ በነፍስና በሥጋ ወደ ሰማያዊ ክብር» እንደተወሰደች ስናስብ ስናሰላስል የቅዱስ ፍራንቺስኮስ የሰላም ጸሎትን የአስተንትኖአችንና የጾማችን ርእስ እንድናደርገው እጋብዛችኋለሁ።

**የሰላም መሳሪያ ለመሆን እንጸልይ**

በሰላም እንድንኖር የጠራን አምላክ (1ቆሮ. 7፡15) « ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ።» ይለናል (ሮም 12፡ 18)። እኛም ምክሩን በመስማት በአንድ ልብ በመሆን በሰላም ከኖርን እርሱ የፍቅርና የሰላም አምላክ ከእኛ ጋር እንደሚሆን በቅዱስ ቃሉ አማካይነት ይነግረናል (2ቆሮ.13፡11)። ለዚህም ነው « ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም። ልባችሁ አይታወክ አይፍራም» የሚለን (ዮሐ. 14፡27)።

ከዚህም በተጨማሪ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ትምህርተ ክርስቶስ ስለ ሰላም እንዲህ ይለናል፣ «የሰብአዊ ሕይወት ክብርና እድገት ሰላምን ይሻል። ጦርነት ባለመኖሩ ወይም የባለጋራዎች ኃይል በመመጣጠኑ ሰላም አለ ማለት አይደለም። እንዲሁም «የሰዎች ጥቅምና በሰዎች መካከል የሚካሄዱ ነጻ ግንኙነቶች በሚገባ ካልተጠበቁ፡ ለሰዎች ሰብአዊ ክብርና ለሕዝቦች ከበሬታ ካልተሰጠ፣በሰዎች መካከል የጋለ ወንድማማችነት ካልተመሰረተ በምድር ላይ ሰላም ሊገኝ አይችልም። ሰላም ሲባል «የስርዓት ርጋታ» ማለት ነው፤ ሰላም የጽድቅ ስራ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬና የፍቅር ውጤት ነው።» (ካ.ቤ.ት.ክ 2304)።

ሰላም ስለተመኘነው ብቻ የሚመጣ ነገር አይደለም የሰላም እንቅፋቶች አሉና ስለዚህ መጸለይና የሰላም መሳሪያ መሆንን ይጠይቃልና፤ የሰላም ጠንቆች የሚባሉት፡ «በሰዎችና በመንግስታት መካከል የሰፈነው ግፍ፡ ከመጠን ያለፈ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ፍትህ መዛባት፡ ቅናት፣አለመተማመንና ትእቢት ሲሆኑ፡ ጦርነቶችንም ያስከትላሉ። ሰላምን ለማስፈን፡እነዚህን ህውከቶች የሚያነሳሱ ሁኔታዎችን ለማስወገድ የሚደረግ ማንኛውም ነገር ሰላምን ለማስፈንና ጦርነትን ለማስቀረት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ያበረክታል (ካቤትክ. 2317)። ስለዚህ እኛም በሚቻለን ሁሉ ከሰዎች ጋር በሰላም ለመኖር ጥረት እንድናደርግና «የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው፥ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና» እንደሚለው (ማቴ. 5፡ 9 ) የሰላም መሳሪያ የሚሆኑ ሰዎችን እንዲያበዛልን እንለምን።

**ጥል ባለበት ፍቅር ይሆን ዘንድ እንጸልይ**

ሰዎች እንደመሆናችን መጠን በተለያዩ ምክንያቶች ልንጣላ እንችላለን፣ ዋናው ነገር ወደቀድሞው ፍቅራችን ለመመለስ መታረቅን መሻት ግድ ይላል። በዚህ የፍልሰታ ጾም ወቅት ጥል ባለበት ሁሉ ፍቅር ይመጣ ዘንድ እንጸልይ። ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናልና ከሁሉ በፊት እርስ በርሳችን አጥብቀን እንድንዋደድ (1ጴጥ. 4፡8)፣ በመዋደድ ውስጥ ተፈላጊው ዋናው ነገር ማእረግ ወይም እውቀት ሳይሆን ስለ ፍቅር ሲባል የሚደረግ ነገር ነው ይለናል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ። «በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሸዋሸዋ ጸናጽል ሆኜአለሁ። ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ። ድሆችንም ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል፥ ሥጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም።» ፍቅር ታጋሽ ነውና እንድንታገስ ቸርነትን እንድናደርግ ቅናትን እንድናስወግድ እንዳንመካ እንዳንታበይ የማየገባ ነገር እንዳናደርግ የራሳችንን እንኳ እንዳንፈልግ እንዳንበሳጭ የተበደልነውን እንዳንቆጥር ከእውነት ጋር እንድንደሰት እንጹም እንጸልይ። ፍቅር ሁሉን ይታገሣል፥ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል» (1ቆሮ. 13፡1-7)።

**በደል ባለበት ይቅርታ እንዲሰፍን እንጸልይ**

መስዋእተ ቅዳሴን ለመካፈል ከመሄዳችን በፊት ካስቀየሙን ሰዎች ጋር እርቅን መፍጠር እንድንችል እንጸልይ። «እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ፥ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ፥ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ፥ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ፥ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ።» (ማቴ 5፡23-24)። የበደሉንን ይቅር በማለት የአምላካችንን ይቅርታ ማግኘት እንድንችል እንጸልይ። «ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ፥ የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋልና፤ ለሰዎች ግን ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ፥ አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም።» (ማቴ 6፡14-15)። ጳውሎስም እንዲህ ይላል፣እናንተ ግን ይቅር የምትሉትን እኔ ደግሞ ይቅር እለዋለሁ፤ እኔም ይቅር ካልሁ፥ ይቅር ያልሁትን ስለ እናንተ በክርስቶስ ፊት ይቅር ብዬአለሁ፥» (2ቆሮ 2፡10)። ስለዚህ እርስበርሳችን ትእግስትን እንድናደርግና በባልንጀራችን ላይ የምንነቅፈው ነገር ካለን ክርስቶስ ይቅር እንዳለን እኛም ይቅር እንድንባባል (ቆላ. 3፡ 13) እንጸልይ።

ኃጢአተኛ መሆናችንን በመረዳት ንስሐ የምንገባበትን ትህትና እንዲሰጠን እንለምን። «ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው። ኃጢአትን አላደረግንም ብንል ሐሰተኛ እናደርገዋለን ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም» (1ዮሐ. 1፡8-10)።

**ጥርጣሬ ባለበት እምነት እንዲገኝ እንጸልይ**

«እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው።» (ዕብ 11፡1) በመሆኑም እግዚአብሔር በእርሱ ለሚታመኑ ሳይቸኩል ሳይዘገይ በእርሱ ጊዜ መልስ ይሰጣል፤ ለዚህም ነው « እግዚአብሔር ግን ዛሬ ያለውን ነገም ወደ እቶን የሚጣለውን የሜዳን ሣር እንዲህ የሚያለብሰው ከሆነ፥ እናንተ እምነት የጎደላችሁ፥ እናንተንማ ይልቁን እንዴት? (ማቴ 6፡30) ዝም ይላችኋል የሚለን። ስንፈራ ደግሞ « እናንተ እምነት የጎደላችሁ፥ ስለ ምን ትፈራላችሁ? በማለት ነፋሱንና ባሕሩን ይገስጻል፥ ሰዎች ነፋሳትና ባሕርስ ስንኳ የሚታዘዙለት፥ ይህ እንዴት ያለ ሰው ነው? እያሉ እስኪደነቁ ድረስ ታላቅ ጸጥታም ይሆናል። » (ማቴ. 8፡26-27)። « ጻድቅ ግን በእምነት ይኖራል ወደ ኋላም ቢያፈገፍግ፥ ነፍሴ በእርሱ ደስ አይላትም።» ( ዕብ. 10፡ 38) የሚል አምላክ «እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ...» ይለናል» (ማቴ. 9፡29)። ምክንያቱም እርሱ « ወደ ልጁ ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብረት የጠራን እግዚአብሔር የታመነ ነው» (1ቆሮ. 1፡9)፤ እኛ ግን እንደ ሐዋርያት ጌታን እምነት ጨምርልን (ሉቃ. 17፡5) እንበለው ምክንያቱም ለሚያምን ሁሉ ይቻላል..እናምናለን አለማመናችንን እርዳው ብለን እንጸልይ (ማር. 9፡23-24)።

**ተስፋ መቁረጥ ባለበት መጽናናት እንዲመጣ እንጸልይ**

በኑሮ ውስጥ ተስፋ የሚያስቆርጡ ነገሮች ያጋጥሙናል፣ አሁንስ ተስፋዬ ማነው የምንልበት ወቅት ይኖራል፤ ይሄኔ ነው አጽናኝ የምንፈልገው፣ የተስፋ ጭላንጭል መኖሩን የሚያመላክተን አምላካችሁ « እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት» (1ጴጥ 5፡7) የሚለንን ሰው ነው የምንሻው።

የመጽናናት አምላክ ሲያጽናናን እኛም ተስፋ የቆረጡትንና ያዘኑትን እንድናጽናና አቅም እንዲጠን እንጸልይ። «የርኅራኄ አባት የመጽናናትም ሁሉ አምላክ የሆነ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ። 4 እርሱ በመከራችን ሁሉ ያጽናናናል፥ ስለዚህም እኛ ራሳችን በእግዚአብሔር በምንጽናናበት መጽናናት በመከራ ሁሉ ያሉትን ማጽናናት እንችላለን። 5 የክርስቶስ ሥቃይ በእኛ ላይ እንደ በዛ፥ እንዲሁ መጽናናታችን ደግሞ በክርስቶስ በኩል ይበዛልናልና» (2ቆሮ. 1፡3-5)። እግዚአብሔር መልካም ነው፥ በመከራ ቀንም መሸሸጊያ ነው፤ በእርሱ የሚታመኑትንም እንደሚያውቅ እንገነዘብ ዘንድ (ናሆም 1፡7) እንጸልይ።

ስለዚህ « ነፍሴ ሆይ፥ ለምን ታዝኛለሽ? ለምንስ ታውኪኛለሽ? የፊቴን መድኃኒት አምላኬን አመሰግነው ዘንድ በእግዚአብሔር ታመኚ» በማለት (መዝ 43፡5) ደካማነታችንን በመቀበል ወደሚያሳርፈን አምላክ እንድንመጣና ልዝብ የሆነው ቀንበሩንና ቀላል የሆነው ሸክሙን ለመሸከም እሺ ማለት እንድንችል በተስፋ እንድንጓዝ እንጹም እንጸልይ (ማቴ. 11፡28-30)። ልባችን ሳይታወክ በእግዚአብሔርና በልጁ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማመን (ዮሐ. 14፡1) እናት ልጅዋን እንደምታጽናና የሚያጽናናንና (ኢሳ. 66፡13) ለዘላለም በማይጥለን አምላክ (ሰቆቃወ ኤርሚያስ 3፡31) እንድንበረታና ልባችን እንዲጠና (መዝ. 31፡24) እንጸልይ እንጹም። «አሁንስ ተስፋዬ ማን ነው? እግዚአብሔር አይደለምን? ትዕግሥቴም ከአንተ ዘንድ ነው» (መዝ. 39፡7)። «ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረት፥ በእርሱም ዘንድ ብዙ ማዳን ነውና እስራኤል በእግዚአብሔር ይታመን» (መዝ. 130፡7)፣ ምክንያቱም «በእግዚአብሔር የታመነ እምነቱም እግዚአብሔር የሆነ ሰው ቡሩክ ነው» (ኤር 17፡7)።

**ሐዘን ባለበት ደስታ እንዲሰፍን እንጸልይ**

የሰው ልጅ ሕይወት በትግል የታጀበ ለመሆኑ ሲናገር ኢዮብ እንዲህ ይላል « በምድር ላይ የሰው ሕይወት ብርቱ ሰልፍ አይደለምን? ወራቱም እንደ ምንደኛ ወራት አይደለምን? 2 ፤ አገልጋይ ጥላ እንደሚመኝ፥ ምንደኛም ደመወዙን እንደሚጠብቅ፥ 3 ፤ እንዲሁ ዕጣዬ የከንቱ ወራት ሆነብኝ፥ የድካምም ሌሊት ተወሰነችልኝ» (ኢዮብ 7፡1-3)። በዚህ ውጣ ውረድ ውስጥ ደስታን መፈለግ ሰውኛ ነው። ነገር ግን ደስታን ያለቦታው መፈለግ ትርፉ ድካም ነው። ስልጣንና ገንዘብ ኃብትና እውቀት የውስጥ ደስታን አይሰጡምና እውነተኛውን ደስታ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆነውን ደስታ ለማግኘት እንጹም። ሰዎች ይህንን ደስታ ይቀምሱት ዘንድ እንጸልይ።

ቃሉ የሚለው « ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ፤ ደግሜ እላለሁ፥ ደስ ይበላችሁ» (ፊል. 4፡4) ስለሆነ ዛሬ ለጌታችን የተቀደሰ ቀን ነው፤ የእግዚአብሔርም ደስታ ኃይላችሁ ነውና አትዘኑ እንደሚል (ነህምያ 8፡10) ዛሬን መደሰት እንድንችል እንጸልይ።

ነገሮች እንዳሰብነው ባይሆኑም ልፋታችን የጠበቅነውን ያህል ባይከፍለንም በአምላካችን መደሰት እንድንችል እንጹም እንጸልይ « ምንም እንኳ በለስም ባታፈራ፥ በወይንም ሐረግ ፍሬ ባይገኝ፥ የወይራ ሥራ ቢጐድል፥ እርሾችም መብልን ባይሰጡ፥ በጎች ከበረቱ ቢጠፉ፥ ላሞችም በጋጡ ውስጥ ባይገኙ፥ 18 ፤ እኔ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል፤ በመድኃኒቴ አምላክ ሐሤት አደርጋለሁ። 19 ፤ ጌታ እግዚአብሔር ኃይሌ ነው፤ እግሮቼን እንደ ዋላ እግሮች ያደርጋል፤ በከፍታዎችም ላይ ያስሄደኛል» (ዕንባቆም 3፡17-19)።

እግዚአብሔር አምላካችን ጸሎታችንን እና ጾማችንን በእናታችን በማርያም አማላጅነት ይቀበልልን!

**የእግዚአብሔር መንግስት ይስፋ! አሜን!**

†ብጹዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነየሱስ ሱራፌል
የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ጳጳስና የኢትዮጵያ ካቶሊካውያን ጳጳሳት ጉባኤ ፕሬዚደንት

ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ከሶሻል ሪሃብሊቴሽን ክፍል ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

**‹‹ ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም። ልባችሁ አይታወክ አይፍራም›› (ዮሐ. 14፡27)**

የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት
Catholic Bishops' Conference of Ethiopia (CBCE)
General Secretariat /ECS
አዲስ አበባ፤ኢትዮጵያ Addis Ababa - Ethiopia

☎ (251) 11-155 03 00
Tel fax (251)11-155 31 13
✉ 2454

E-Mail: CBCE@cbce-gs.org
cbce.ecs@gmail.com
website: www.cbce-gs.org

ቀን Date: ሐምሌ 16 ቀን 2016 ዓ.ም
ቁጥር Ref: CBCE/GS/238/2024

ለድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት
ድሬዳዋ

ጉዳዩ፡ የአብሮነት መልዕክት ስለማስተላለፍ

የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ሰኔ 25 ቀን 2016 ዓ.ም በድሬዳዋ አስተዳደር "አሸዋ ገበያ" ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በተከሰተው የእሳት አደጋ እጅግ ማዘኗን ትገልጻለች። አደጋው ምንም እንኳን በሰው ሕይወት ላይ አደጋ ባያደርስም ለብዙ የከተማው ነዋሪዎች መተዳደሪያ በሆነ ቦታ ላይ በመከሰቱ ከፍተኛ አኮኖሚያዊ ቀውስ እንዳስከተለ እና ወደፊትም እንደሚያስከትል ተረድተናል።

በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የሀረር ሀገረስብከት ጽ/ቤት፣ ካህናት እና የሥራ ኃላፊዎች አደጋው በተከሰተበት ቦታ በመገኘት ቤተክርስቲያናችን ከድሬዳዋ አስተዳደር ጎን መሆኗን ያረጋገጡ ሲሆን እኔም በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ስም በአደጋው የተሰማኝን ሀዘን እየገለጽኩ አስተዳደሩ ለተፈጠረው አደጋ ለሚያደርገው ተግባር ቤተክርስቲያናችን ከጎናችሁ እንደምትቆም በአክብሮት እገልጻለሁ።

መላው ካቶሊካውያን እና በጎ ፍቃድ ያላችሁ ሁሉ በአደጋው ጉዳት ለደረሰባቸው የመልሶ ማቋቋም ሂደት አቅማችሁ በሚፈቅደው ሁሉ እንድትተባበሩም ጥሪ አቀርባለሁ።

ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይባርክ !

+ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነየሱስ
ሊቀጳጳሳት ዘካቶሊካውያን
የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ፕ...

ግልባጭ፣
በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የሀረር ሀገረስብከት ጽ/ቤት

...rchbishop of Addis A...
Chairman of Ethiopian Reconciliation and Peace Commission; Fr.Teshome F...
Please do not address your reply to a particular individual but to CB...

# የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ሊቀጳጳስ እና የጳጳሳት ጉባኤ ፕሬዚዳንት ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነየሱስ በድሬዳዋ አስተዳደር "አሸዋ ገበያ" ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በተከሰተው የእሳት አደጋ ማዘናቸውን ገለፁ

ብፁዕ ካርዲናል ለድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት የአብሮነት መልዕክታቸውን በፅሁፍ ያስተላለፉ ሲሆን በመልዕክታቸውም ሰኔ 25 ቀን 2016 ዓ.ም በድሬዳዋ አሸዋ ገበያ በተፈጠረው ድንገተኛ የእሳት አደጋ እጅግ ማዘናቸውን ገልፀዋል። የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን በዚህ አደጋ፥ ከአስተዳደሩ ጎን እንደሚቆሙ አስታውቀዋል። በተጨማሪም በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የሀረር ሀገረስብከት ጽ/ቤት፣ ካህናት እና የሥራ ኃላፊዎች አደጋው በተከሰተበት ቦታ በመገኘት ቤተክርስቲያናችን ከድሬዳዋ አስተዳደር ጎን መሆኗን ማረጋገጣቸውን ገልፀዋል።
ብፁዕ ካርዲናል መላው ካቶሊካውያን እና በጎ ፍቃድ ያላቸው ሁሉ በአደጋው ጉዳት የደረሰባቸውን መልሶ የማቋቋም ሂደት ያቅማቸውን በማድረግ እንዲተባበሩ ጥሪ አቅርበዋል።



የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት
Catholic Bishops' Conference of Ethiopia (CBCE)
General Secretariat /ECS
አዲስ አበባ፤ኢትዮጵያ Addis Ababa - Ethiopia

☎ (251) 11-155 03 00
Tel fax (251)11-155 31 13
✉ 2454

E-Mail: CBCE@cbce-gs.org
cbce.ecs@gmail.com
website: www.cbce-gs.org

ቀን Date: ሐምሌ 18 ቀን 2016 ዓ.ም
ቁጥር Ref: CBCE/GS/241/2024

ለደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ ዞን

ጉዳዩ፡ የአብሮነት መልዕክት ስለማስተላለፍ

የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ሐምሌ 16 ቀን 2016 ዓ.ም በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ ዞን፣ ገዜ ጎፋ ወረዳ፣ ኬንቾ ሻቻ ጎዝዲ ቀበሌ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በመሬት መንሸራተት ምክንያት በተከሰተው አደጋ እጅግ ማዘኗን ትገልጻለች። አደጋው ክቡር በሆነው በሰው ልጅ ሕይወት ላይ ከፍተኛ አደጋ ያደረሰ በመሆኑ ኃዘናችን ጥልቅ ነው። በዚህ አስከፊ አደጋ ሕይወታቸውን ያጡትን ዜጎች ለነፍሳቸው እረፍት እየጸለይን በአደጋው ቤተሰቦቻቸውን እና ወዳጅ ዘመዶቻቸውን ላጡ ሁሉ ቤተክርስቲያናችን መፅናናትን ትመኛለች።
በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት የልማት ሥራ ኃላፊ፣ የሶዶ ሀገረስብከት ካህናት እና የሥራ ኃላፊዎች፣ የካቶሊክ ተራዲኦ ድርጅት የሥራ ኃላፊዎች አደጋው በተከሰተበት ቦታ በመገኘት የአደጋውን አስከፊነት ተመልክተዋል። በርካቶች ልጆቻቸውን፣ እናቶቻቸውን፣ አባቶቻቸውን አጥተዋል። አደጋው አፋጣኝ የነፍስ ማዳን እና የሰብዓዊ ድጋፍ ስለሚያስፈልግ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ስም በአደጋው የተሰማኝን ኃዘን እየገለጽኩ ዞኑ ለተፈጠረው አደጋ ለሚያደርገው ተግባር ቤተክርስቲያናችን ከጎናችሁ እንደምትቆም በአክብሮት እገልጻለሁ።
መላው ካቶሊካውያን እና በጎ ፍቃድ ያላችሁ ሰዎች ሁሉ በአደጋው ጉዳት ለደረሰባቸው የመልሶ ማቋቋም ሂደት አቅማችሁ በሚፈቅደው ሁሉ እንድትተባበሩም ጥሪ አቀርባለሁ።
ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይባርክ !

+ ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነየሱስ
ሊቀጳጳሳት ዘካቶሊካውያን
የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ፕሬ...

ግልባጭ፣
በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የሶዶ ሀገረስብከት ጽ/ቤት

...rchbishop of Addis Ababa, President of the **CBCE,**
Chairman of Ethiopian Reconciliation and Peace Commission; Fr.Teshome Fikre (PhD), Secretary General
Please do not address your reply to a particular individual but to CBCE General Secretariat

## የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ...

ከገፅ 1 የዞረ

ብፁዕ ካርዲናል ለደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት የአብሮነት መልዕክታቸውን በፅሁፍ ያስተላለፉ ሲሆን በመልዕክታቸውም በዞኑ ወረዳ ኬንቾ ሻቻ ጎዝዲ ቀበሌ በተከሰተው እጅግ አሳዛኝ የመሬት መንሸራተት አደጋ እጅግ ማዘናቸውን ገልፀዋል።
በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት የልማት ሥራ ኃላፊ አቶ በቀለ ሞገስ፣ የሶዶ ሀገረስብከት ካህናት እና የሥራ ኃላፊዎች፣ የካቶሊክ ተራዕዶ ድርጅት የሥራ ኃላፊዎች አደጋው በተከሰተበት ቦታ በመገኘት የአደጋውን አስከፊነት ተመልክተዋል። በርካቶች ልጆቻቸውን፣ እናቶቻቸውን፣ አባቶቻቸውን እና በርካታ ቤተሰቦቻቸውን ማጣታቸው ተገልጿል።
አቶ በቀለ አደጋው እጅግ ከባድ መሆኑን መመልከታቸውን ገልጸው አፋጣኝ የሰብዓዊ ድጋፍ እንደሚያስፈልግ በመረዳት የካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ከሶዶ ሀገረስብከት እና ከካቶሊክ ተራዕዶ ድርጅት እና ሌሎች አጋሮች ጋር በመተባበር የአደጋ መከላከል እና የሰብዓዊ ድጋፍ ለማድረግ ጥረት መጀመራቸውን ገልጸዋል።
ብፁዕ ካርዲናል አደጋው አፋጣኝ የነፍስ ማዳን እና የሰብዓዊ ድጋፍ የሚያስፈልገው በመሆኑ ዞኑ ለተፈጠረው አደጋ ለሚያደርገው ተግባር ቤተክርስቲያናችን ከጎን እንደምትቆም ገልጸው መላው ካቶሊካውያን እና በጎ ፍቃድ ያላቸው ሰዎች ሁሉ በአደጋው ጉዳት የደረሰባቸውን መልሶ የማቋቋም ሂደት የአቅማቸውን በማድረግ እንዲተባበሩ ጥሪ አቅርበዋል።



‹‹ሰው ሆይ፤ መልካም የሆነውን አሳይቶሃል፤ እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ምንድን ነው?
ፍትሕን ታደርግ ዘንድ፣ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ፣ በአምላክህም ፊት በትሕትና ትራመድ ዘንድ አይደለምን?›› (ሚኪያስ 6፡8)

## በኢትዮጵያ የአገልግሎት ...

ከገፅ 1 የዞረ

መድኃኔዓለም ቤተ ክርስያቲያን በተደረገው የምስጋና ቅዳሴ መርሃ ግብር ብፁዕ ሊቀ ጳጳስ አንቶንዮ ካሚሌሪ የቅድስት መንበር እንደራሴ በኢትዮጵያ የምትገኘውን ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ማህበረሰብ አመስግነዋል። በኩላዊት ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ በእንደራሴነት ተመድቤ ባሳለፍኩት አራት ዓመት ለተደረገልኝ የሥራ ትብብርና ቀና መንፈስ ምስጋና እያቀረብኩ ይህ የኢትዮጵያ የእንግዳ ተቀባይነትና ቤተሰባውነት ያለኝን አክብሮቴን እገልፃለሁ ብለዋል። በቆየሁበት የአገልግሎት ዘመን ሁሉንም ሀገረ ስብከት ተዘዋውሬ የተመለከት ሲሆን ለአገልግሎታችሁ ታላቅ ክብር አለኝ ብለዋል። በዚሁ የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብን እያመሰገንኩ እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ ብለዋል። የመጪው የአገልግሎቴ ቦታ በኩባ ሀገር መሆኑን በመግለጽ በፀሎታችሁ አስቡን ብለዋል።

በዚሁም ጊዜ ብፁዕ ካርዲናል ብርሃነየሱስ ሊቀ ጳጳሳት ዘካቶሊካውያን ብፁዕነታቸው በአምባሳደር ደረጃ በሀገራችን ላበረከቱት አገልግሎት በኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት ጉባኤና በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ማህበረሰብ ስም ምስጋና አቅርበዋል። የቅድስት መንበር እንደራሴ በሀገራችን መኖር ታላቅ በረከት መሆኑን በመግለጽ ለኛ ለካቶሊካውን ብቻ ሳሆን ለሰው ልጅ በሙሉ ነው ብለዋል። በሚሄዱበት የአገልግሎት ቦታ መልካሙን ሁሉ እንደሚመኑላቸው ገልፀዋል።

ይህን የምስጋና ቅዳሴ ያዘጋጀው በኢትጵዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲን ገዳማት የበላይ ጽህፈት ቤት ነበር።



## የቅዱስ ዮሐንስ ጳውሎስ...

ከገፅ 1 የዞረ

በአዲስ አበባ ከተማ በልደተማርያም ካቴድራል ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ የሚገኘው ይህ ማዕከል ሐምሌ 6 ቀን 2016 ዓ.ም. ብፁዕ ካርዲናል ብርሃነየሱስ ሊቀ ጳጳሳት ዘካቶሊካውያን ዘኢትዮጵያ ተባርኮ አገልግሎቱን ለማስተዋወቅ ይፋ የተደረገበት ነበር። በሥነ ሥርዓቱ ላይ እና ጥሪ የተደረገላቸው የገዳማት ኃላፊዎችና የመንግሥት ተወካይ፣ የቁምሰና ተወካዮች እንዲሁም እንግዶች ተገኝተዋል።

ስለ ማዕከሉ አጠቃላይ ሁኔታ ክቡር አባ ጴጥሮስ በርጋ ከጅማሬው መነሻ ሀሳብ ጀምሮ አሁን የደረሰበት መልካምና ተስፋ ሰጪ ሁኔታን በማዕከሉ በሥራ ሂደቱ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን በተመለከት ለእንግዶች ገለፃ አድርገዋል። ቤተክርስቲያን የወጣቶችን ጥያቄ ለመመለስ ለምታደርገው አገልግሎት ይህ ሙያዊ ሥልጠና ማዕከል መመስረተ ትልቅ እገዛ እንዳለው ገልጻዋል። ለዚሁ የሁሉ ወገን ትብብር ወሳኝ መሆኑን ገልጸዋል።

የማዕከሉን ዳሬክተር ኢንጂነር ዘካርያስ ቤተክርስቲያን ለወጣቶች መልስ ለመስጠት በየሰበካው የምታደርገውን የተለያየ ሙያዊ ሥልጠና እንዳለ ሆኖ አሁን ሊጀመር የታቀደው ተጨማሪና በአብዛኛው ከዚህ በፊት ያልተጀመረ እንደሆነ ገልፀዋል። በቅርቡ በአራት በተለያየ ሙያ ዘርፍ ትምህርት ለመጀመር ዝግጅት እየተደረገ እንደሆነና ማዕከሉ ቀስ በቀስ የተለያዩ የሙያ ሥልጠናዎችን በመጨመር ለወጣቱ ሙያዊ ክህሎት እና በራስ መተማመን እንዲያጎለብቱ የተቻለውን ሁሉ ለማድረግ እንደሚጥር ኢንጂነር ዘካርያስ ገልፀዋል።

ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶችም ባደረጉት ንግግር ማዕከሉ መቋቋም ለወጣቶች ሥራ ፈላጊዎች ታላቅ እገዛ እንደሚደርግ ገልጸው ቤተክርስቲያን በመንፈሳዊ የምታደርገውን አገልግሎት በተጨማሪ በሰው ልማት ላይ መሥራት ራሱ የመንፈሳዊ አገልግሎት አካል ነው ብለዋል።

ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነየሱስ ማዕከሉን ተዘዋውረው በማየትና በመባረክ የተሰማቸውን ደስታ የገለፁ ሲሆን። የማዕከሉ ዕድገት ከመጀመሪያ ጊዜ አንስቶ እንደሚከታተሉ ገልፀው በገንዘባቸው፣ በሃሳባቸው፣ በጉልበታቸው ይህ ማዕከል ዕውን እንዲሆን ድጋፍ ያደረጉትን ወገኖች ሁሉ አመስግነዋል። ቤተክርስቲያን ለወጣቶች ያላትን ፍቅር ገልፀው በተለያዩ ሙያ የሰለጠኑ ወገኖች ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን ለሀገራችን ዕድገት ወሳኝ ኃይል መሆናቸውን ተናግረዋል። ቤተ ክርስቲያንም የሰው ልጅ በመንፈሳዊና በአካል እድገት ማደግ አለበት ብላ የምታምን በመሆንዋ ይህ አይነት አገልግሎት መስጠትዋን ትቀጥላለች ብለዋል። በመጨረሻም ለማዕከሉ እዚህ ደረጃ መድረስ በግንባር ቀደም የደከሙትን አባ ጴጥሮስ በርጋን አመስግነል። ማዕከሉ በሙዚቃ፣ በኮምፒተር ሳይንስ (IT)፣ በቪዲዮ ግራፊ፣ በህንፃ ጥገና ሙያ ሥልጠና እንደሚጀምር በዕለቱ ተገልጻል። ማዕከሉ በተመረጡት ሙያ ልዩ ችሎታ ዕውቀተ ባላቸው መምህራን ለማስተማር ዝግጅቱን እያጠናቀቀ እንደሚገኝ ተገልጻል። በቅርቡ ማዕከሉ በሚያስቀምጠው መስፈርት ምዝገባ እንደሚጀመርና ቁምስናዎች በሚሰጣቸው ኮታ ወጣት ልጆቻቸውን ለማስተማር የራሳቸውን ዝግጅት እንዲያደርጉ ጥሪ እንደሚያቀርብ ተገልጿል።



## የቅዱስ ጴጥሮስ መንበር...

ከገፅ 1 የዞረ

ጉባኤው በቀሪው ጊዜያት በቅድስት መንበር ከሚገኙት ከፍተኛ የቤተክርስቲያን ጽ/ቤቶች ጋር ተከታታይ ስብሰባዎች አድርጓል። ሰኔ 18 ቀን 2016 ዓ.ም. በቫቲካን የሚገኘውን የወገነ ክህነት ጽ/ቤት ተገኝተው በኢትዮጵያ የካህናት እንቀስቃሴ ፤ የህንጻት እና የብቃት ዝግጅት ላይ ያተኮረ ውይይት ፤ በመቀጠልም የስብከተ ወንጌል ጽ/ቤት አዳዲስ የስብከተ ወንጌል አማራጮች፣ የኢትዮጵያ ካህናት ተግዳሮቶች እና የወደፊት አቅጣጫዎችን በተመለከተ የበለጠ ለማጠናከር ውይይት አድርገዋል።

ሌላው በቫቲካን የሚገኘውን የቤተክርስቲያን ከፍተኛው ፍርድ ቤት ጽ/ቤት ተገኝተው በተለይም የቤተክርስቲያን የፍትህ አስተዳደር ጉዳዮችን እና የጋብቻ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን የሚመለከተው ውይይት አድርገው በዕለቱ ማጠቃለያም በቅዱስ ጳውሎስ ባዚሊካ የመስዋዕተ ቅዳሴ እና የጸሎት መርሃግብር ተደርጓል።

በፁዓን ጳጳሳት በቫቲካን የሚያደርጉትን የጋራ ጉብኝት በመቀጠል በቫቲካን ከመቶ ዓመት በላይ ባስቆጠረው በኢትዪጵያ ኮሌጅ በመገኘት ከኮሌጁ ኃላፊዎች እና ተማሪዎች ጋር የአብሮነት ቆይታ አድርገዋል። በቅርቡ 25 ዓመት የብር ኢዮቬልዩ ያከበሩት የኮሌጁ አባቶችም ከብፁዓን ጳጳሳት ቡራኬ ተቀብለዋል።

ይህ የአድ ሊሚና ጉብኝት በልዩ መልኩ ላለፉት አራት ዓመታት በሀገራችን በነበረው የሰላም እጦት እና ጦርነት ምክንያት በጉባኤዎች ላይ መገኘት ያልቻሉት ብፁዕ አቡነ ተስፋስላሴ የአዲግራት ሀገረስብከት ጳጳስ በተገኙበት የተደረገ በመሆኑ መላው የኢትዮጵያ ጳጳሳት በሙላት እና በህብረት ለቤተክርስቲያን እና ለሀገር ሰላም የሚጸልዩበት ነበር።







# የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የሶዶ ሀገረስብከት የልማት ጽ/ቤት ልዑካን ቡድን የብፁዕ አቡነ ስዩም ፍራንሷን ጥሪ በመቀበል ወደ ጎፋ ዞን አቀና

በሶዶ ሀገረስብከት የልማት ጽ/ቤት ዳይሬክተር አቶ ሙሉነህ ተስፋዬ የተመራው የልዑካን ቡድን የኢትዮጵያ ካቶሊክ ጽ/ቤት ዳይሬክተር አቶ በቀለ ሞገስ፣ ከካቶሊክ ተራድኦ ድርጅት (CRS) የመጡ እንግዶችን እና የሀገረስብከቱ ERT (Emergency Response Team) ቡድን ይዞ ወደ ስፍራው አቅንተዋል።

በቆይታቸውም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ስብሰባ አድርገዋል። እነኝህም OCHA, IOM, UNCIEF, WHO, UNFPA, WFP, World Vission እና Red Cross ናቸው። በውይይታቸውም ለተጎዱ አካላት እና ለማህበረሰቡ መደረግ ያለበት ሰብዓዊ ድጋፍ ላይ ከስምምነት ደርሰዋል።




ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ከፍትህና ሰላም ክፍል ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው።

‹‹ጌታ ለሚፈሩት ወዳጃቸው ነው›› (መዝ. 25፡14)



በክቡር አባ አብነት አበበ
ዘማኅበረ ልኡካን/ ላዛሪስት

# መልካምን ለመስራት እግዚአብሔርን መፍራት

*ሁላችንም በራሳችን መንገድ መልካም ነገርን እናደርጋለን፤ ነገር ግን የሚያነሳሳን ምክንያት ምንድን ነው ብለን ስንጠይቅ በተለምዶ ሶስት ምክንያቶችን እናገኛለን፤ እነርሱም፡ ግዴታችን/ኃላፊነታችን ስለሆነ፣ ሽልማትን ለማግኘት ወይም ቅጣትን ከመፍራትና በመጨረሻም ለፍቅር ብለን ስለምንሰራ የሚሉት ናቸው። ዝርዝሩን እንመልከት።*

1) **ግዴታ/ኃላፊነት/፡** ለምሳሌ ነርሶች ስራቸውን የሚሰሩት ራሳቸውን በመስጠት ነው፤ ለምን፤ እንደ ክርስቲያን በእሁድ ዕለት ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድ እናስቀድሳለን እናመልካለን ግን ለምን፤ ሰው ሲሞት ለቅሶ እንደርሳለን፤ ለምን፤አብዛኛውን ጊዜ የምናደርጋቸውን ነገሮች የምናደርገው መደረግ ስላለበት ወይም ግዴታ ስለሆነብን ነው።

**2) ሽልማት ለማግኘት ወይም ከቅጣት ለማምለጥ**

ከልጅነታችን ጀምሮ ከተለማመድናቸው ነገሮች አንዱ ስለሚሰጠን ነገር ስንል የታዘዝነውን ነገር ማድረግን ነው፤ ለምሳሌ በትምህርታችን ጥሩ ውጤት ካመጣን ወይም በጥሩ ውጤት ካለፍን ሽልማት እንደሚሰጠን ሲነገረን ለሽልማቱ ስንል እንሰራለን፤ አትሰረቅ፤ እግዚአብሔር ሺ ዓይኖች ስላሉት ያይሃል፤ እናም ወደ ገሀነም ይከትሃል፤ ጌታ ሆይ እኛ ሁሉንም ነገር ትተን ተከተልንህ፤ ታዲያ የምናገኘው ምንድን ነው ከሚሉት አባባሎች ጀርባ ሽልማትን ፍለጋ ወይም ቅጣትን ለመሸሽ እንደምናደርግ ያሳያሉ።

**3) ፍቅር**

ለምናደርገው መልካም ስራ ሌላው ምክንያት ፍቅር ነው። ሰዎች ሲቸገሩና የእኛን እርዳታ ሲፈልጉ ከእነርሱ ምንም ሳንጠብቅ ስለ ሰው ልጆች ፍቅር ስንል የምንሰጠው አገልግሎት ነው። ስለ ፍቅር ስንል የምናደርግ ከሆነ (በውስጣችን ፍቅር ሲኖር) ፍላጎታችንና ኃይላችን/የማድረግ አቅማችን ይጎለብታል፤ በዚህ ምክንያት ለሌላው ማደግ ስንል መርዳት እንፈልጋለን ወደንና መርጠን እናደርጋለን።

ዛሬ በአገራችን ኢትዮጵያ በብዙዎቻችን ዘንድ በሚባል መልኩ የመልካም ስራ ተካፋይ ለመሆን ስራችንን በኃላፊነት የመወጣት ስሜት ጠፍቶ ሽልማትን መሻት ይቅርና ላጎደልነው በጎ ተግባር በፈጣሪ ፊት እንደምንጠየቅ ተዘንግቶ ከዚህም ባሻገር ስለሞያችን ወይም ስለምናገለግለው ህዝብ ፍቅር ስንል መስራት ጊዜው ያለፈበት እስኪመስል ድረስ ከመልካም ስራ መራቃችን እንዲሁም በመካከላችን ያለው ጦርነትና ጠብ (ያዕ.4፡1) የስጋ ሥራ የሆኑት ‹ዝሙት፡ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣኦትን ማምለክ፣ አስማት፣ ጠላትነት፣ ጠብ፣ ቅናት፣ ቁጣ፣ አድመኛነት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ መሶልሶል (ቅጥ ያጣ ፈንጠዝያ/ ልቅ የሆነ ወሲባዊ ተግባር የሚፈጸምበት ድግስ)...(ገላ. 5፡19-21) በመካከላችን ተንሰራፍቶ ስናይ ለእኩይ ተግባር አደላችሁ ያስብላል።

የካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የነገረ መለኮት (የካቶሊክ ቲኦሎጂ) ሊቅ የሆነው ዶክተር እስኮት ሃን በአንድ ወቅት ሲያስተምር ክርስቲያናዊ ቤተሰብ ከውስጥና ከውጭ ስላለበት ጫና የሚከተለውን ጠቅሶ ነበር፤ ይህም የዘመኑ ቤተሰብ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የዚህ ጫና ተጠቂ መሆኑን ያመለክታል።

በምንኖርበት ማኅበረሰብ ውስጥ (በባህላችን) ቁሳዊ ኃብትን ማፍቀር ተመለከ፤ግብረ ገብ አልባነት ማራኪ ተደረገ፤ እውነት መነመነች፤ ኃጢአት የተለመደ (ቀላል) ነገር ሆነ፤ ትዳርን ማፍረስ (መፋታት) በምክንያታዊነት ተደገፈ፤ ጽንስ ማስወረድ ሕጋዊ ተደረገ፤ በቴሌቭዥንና (በመረጃ መረብ ትስስር እና) በፊልሞች የሚታዩ ወንጀሎች ህጋዊ ፈቃድ ተሰጣቸው፤ እጾችን (ሃሽሽ) መጠቀም ቀላል እንዲመስል ተደረገ፤ ቀልዶቻችን ከመስመር ወጡ (ቅጥ አጡ)፤ መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ልበ ወለድ ተቆጠረ፤ ቤተክርስቲያን ተቀለደባት ፤ እግዚአብሔር ወደ ጎን ተተወ፤ ክርስቲያኖች እንደ ሰይጣን (ክፉ/መጥፎ) ተቆጠሩ፤ አረጋውያን እንደ ሰው የሚገባቸውን ክብር አጡ (ከሰው በታች ተቆጠሩ)፣ የመዳን ተስፋ የሌላቸው ሕሙማን እንዲሞቱ ተደረገ፤ ድሆች ተበደሉ፤ የአእምሮ ሕሙማን ተገለሉ፤ ልጆቻችን ፍዝዝ ድንዝዝ እንዲሉ ተደረጉ፣ በቤታችን ውስጥ ጸባያችን ስርአት አልበኝነትን አነገበ፤ ንግግራችን እኛን የማይመጥን ሆነ፤ እምነታችን ዓለማዊ መንፈስን ተላበሰ፤ ሁሉም ነገር ገንዘብ የማግኛ መንገድ ሆነ፤ እኛ ክርስቲያኖች መገኘት በሌለብን ቦታ (ሁኔታ) ውስጥ ሆነን ብዙ ጊዜ ተገኘን፤ እረኞቻችን ተስፋ ቆረጡ(ሞራላዊ ሕይወታቸው ዝቅ አለ)፤ እምነታችን ተከፋፈለ፤ ስለዚህ ክርስቲያናዊ ምስክርነታችን ተአማኒነትን አጣ። ታድያ ምን እናድርግ በማለት ይጠይቅና ምላሹን እንዲህ ሲል ያቀርባል፣ አምልኮአችንን ሕይወት እንዝራበት፤ ልዩነታችንን እናጥብበው፤ የተኙ ምእመናንን እንቀስቅሳቸው፤ ቤተሰባዊ ሕይወታችን ይታደስ፤ እንደገና ስብከተ ወንጌል ያሻናል ብሏል አሜሪካዊው ዶክተር እስኮት። እኛም ዛሬ ጥያቄአችን ከመጥፎ ስነ ምግባራችን ተላቀን የመልካም ስራ ተካፋዮች ለመሆን «ጌታ ሆይ፤ ምን ላድርግ?» (ሐዋ.ሥ 22፡10) በማለት እግዚአብሔር አምላካችን ከእያንዳንዳችን ምን እንደሚፈልግ ልንጠይቅ ግድ ይለናል።

## እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ምንድን ነው?

### እርሱን እንድንፈራው፣ እንድንታዘዘው፣ እንድንወደውና እንድናገለግለው ይፈልጋል

«እስራኤል ሆይ፤ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ምንድን ነው? አምላክህን እግዚአብሔርን እንድትፈራው፣ በመንገዶቹ ሁሉ እንድትሄድ፣ እንድትወድደው፣ በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ እንድታገለግለው፣ መልካም እንዲሆንልህና ዛሬ እኔ የምሰጥህን ትእዛዞችና ሥርዐቶች እንድትጠብቅ አይደለምን?» (ዘዳ. 10፡12-13)።

### ፍትህ ምህረትና ትህትናን ከእኛ ይሻል

«ሰው ሆይ፤ መልካም የሆነውን አሳይቶሃል፤ እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ምንድን ነው?

ፍትሕን ታደርግ ዘንድ፣ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ፣በአምላክህም ፊት በትሕትና ትራመድ ዘንድ አይደለምን?»(ሚኪያስ 6፡8)

## እግዚአብሔርን መፍራት (1ጴጥ. 2፣17)

### እግዚአብሔርን መፍራት እርሱ ታላቅ አምላክ፡ ኃያልና የሚያስፈራ መሆኑን ከመረዳት ይመነጫል

እግዚአብሔር ስለ እኛ ያለውን ምህረት መረዳት ስንጀምር እውነተኛ ፍቅር ምን መሆኑንና እግዚአብሔር ምን ያህል ጥልቅ በሆነ ፍቅር እንደሚወደን ማየት እንችላለን። በምህረቱ ፊት ስንሆን እርሱ ምን ያረገን ይሆን (ምን ይደርስብን ይሆን) የሚለው ፍርሀት ይለወጥና እርሱን ወደማክበርና በእርሱ ወደመደነቅ ውስጥ እንገባለን። እንደ ኃጢአታችን ቢሆን ኖሮ ቅጣቱ የከፋ ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ለሚፈልጉት ሁሉ ፍቅሩንና ምህረቱን ማሳየት መረጠ፤ወደደ። «እግዚአብሔርን የሚፈሩ እነማን ናቸው? እነርሱ መከተል የሚገባቸውን አካሄድ እንዲመርጡ እርሱ ያስተምራቸዋል» (መዝ. 25፡12)

### እግዚአብሔርን እንደማንነቱ ስናውቀው ለእርሱ ያለን የአክብሮት ፍርሃታችን ይጨምራል

እግዚአብሔርን መፍራት ማለት እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ማወቅ ማለት ነው፤ ይኸውም እርሱ ቅዱስና ሁሉን ቻይ ጻድቅና ሁሉን አዋቂ ጥበበኛ መሆኑን መረዳት ማለት ነው።

የእግዚአብሔርን ማንነት በትክክል ስንረዳ፡ የራሳችን እውነተኛ ማንነት ማለትም ኃጢአተኛና ደካማ፡ ያለ እርሱ ምንም እንዳልሆንንና ምስኪንነታችን ይገለጥልናል። የእግዚአብሔርና የእኛን ማንነት ስንረዳ (የእርሱን ታላቅነትና የእኛን ኢሚንትነት ሲገባን) በእግሩ ስር በትህትና ተደፍተን አክብሮታችንን እንገልጽለታለን፤ ያን ጊዜ ነው እርሱ የመረጠውን መንገድ የሚያሳየን።

### እግዚአብሔርን መፍራት እርሱን ይበልጥ ወደማወቅ ደረጃ ያመጣናል

«ጌታ ለሚፈሩት ወዳጃቸው ነው» (መዝ. 25፡ 14) እንደሚለው ትልቅ ክብር የሚሰጡትን ወደ ራሱ ያቀርባቸዋል ለዘላቂ ወዳጅነት ይጋብዛቸዋል። ከአምላክ/ከፈጣሪ ጋ/ ያለንን ወዳጅነት የሚተካከል/የሚወዳደር/ የለምና እርሱን ባከበርነው ቁጥር ከእርሱ ጋር ያለን ዘላለማዊ ወዳጅነታችን ያድጋል።

### እግዚአብሔርን መፍራት ማለት በእርሱ ምክንያት ፍርሃት ውስጥ መግባት ማለት አይደለም

ሙሴም ለህዝቡ እንዲህ አላቸው፡ «አትፍሩ፡ ሊፈትናችሁ ኃጢአትንም እንዳትሰሩ እርሱን መፍራት በልባችሁ እንዲሆን እግዚአብሔር መጥቷልና» (ዘጸ. 20፡20)።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ስፍራ «አትፍሩ» የሚል ቃል እናገኛለን። ይህም ያለው እግዚአብሔር ሕዝቡን ማስፈራራት ፈልጎ ሳይሆን እስራኤላውያን ታላቅ ኃይሉን በመመልከት እውነተኛ አምላክ መሆኑን እንዲያውቁና እንዲታዘዙት ለማድረግ ነበር፤ በሚታዘዙበት ሰዓት የእርሱ ኃይል አብሮአቸው እንዲሆን ፈቃዱ ነበር። እግዚአብሔር ከፍርሃት ይልቅ በፍቅር እንድንከተለው ይፈልጋል፤ ፍርሃትን ለማሸነፍ ፍቅሩን ይበልጥ ማሰብ ይኖርብናል፤ ምክንያቱም «ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም» (1ዮሐ. 4፡18)።

## ጥበብን ፍለጋ

«የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት » (ምሳሌ. 1፡7) ከሆነ ጥበብ ማናት? ምንድን ናት? እንዴትስ ትገኛለች? የጥበብ ፍሬዎችና እሴቶች ምን ምን ናቸው?

**ጥበብ ማለት**

«የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፤ ሰነፎች ግን ጥበብንና ተግሣጽን ይንቃሉ»(ምሳሌ. 1፡7) እንደሚለው ጥበብ ማለት እውቀትን በትክክል መጠቀም ማለት ነው። ማወቅ ማለት ጥበበኛ መሆን ማለት አይደለም፤ ጥበበኛ የሚያሰኘን እውቀትን በትክክለኛው መንገድ መጠቀም ስንችል ነው። ጥበብ ማለት ሕዝብን ለማስተዳደር (በትክክል ለመፍረድ) መልካሙንና ክፉውን መለየት የሚያስችል አስተዋይ ልቡና ማለት ነው። (1ነገ 3፡9)።

**ጥበብን ለማግኘት**

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ጥበብ የሚገኘው ከእግዚአብሔር ሲሆን እርሱ ጥበብን የሚሰጠው ለሚጠይቁት ሰዎች ነው።

ወደ ገፅ 7 ዞሯል

ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ሐዋርያዊ ሥራዎች ኮሚሽን ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

**‹‹እስራኤል ሆይ፤ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ምንድን ነው? አምላክህን እግዚአብሔርን እንድትፈራው፣ በመንገዶቹ ሁሉ እንድትሄድ፣ እንድትወድደው፣ በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ እንድታገለግለው፣ መልካም እንዲሆንልህና ዛሬ እኔ የምሰጥህን ትእዛዞችና ሥርዐቶች እንድትጠብቅ አይደለምን?›› (ዘዳ. 10፡12-13)**

# የማይቀየረው እውነታ

## ክፍል ሁለት

(በክቡር በአባ ምሥራቅ ጥዩ)

> "በእርግጥም የእውነት መሠረቱ መለኮት ነው፤ በየትኛውም ዓይነት ምድራዊ ኃይልና ሥልጣን የማይሸረሸር ነው።"

ካለፈው ዕትም የቀጠለ



### የማይቀየረው እውነታና የተመሳሳይ ፆታ ጥምረት

በቅርብ ጊዜያት በብዙዎች ዘንድ ከሚናፈሱት የተዛቡ ወሬዎች መካከል አንዱ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የተመሳሳይ ፆታ ጋብቻ በቤተ ክርስቲያን እንዲደረግ ልትፈቅድ ነው፤ ተመሳሳይ ፆታ ሆነው የተጋቡት በጉዲፈቻ መልክ ልጅ እንዲያሳድጉ የሚፈቅድላቸውን ሕግ ልትቀበል ነው የሚሉትና ተመሳሳይነት ያላቸው አስተያየቶች በማኅበራዊ ሚዲያ በኩል ሲነገርና ሲራገብ እየሰማን ነው። አንዳንድ ዜና ማሰራጫዎች ደግሞ የሕዝቡን ትኩረት ለመሳብና ብዙ ተመልካች ለማፍራት በማለት ይህንን አጀንዳ በካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለውይይት እንደቀረበ አድርገው ሲነዙት ነበር።

በእርግጥ የዚህ ወሬ ሁሉ አንዱ ምክንያት የሆነው እ.አ.አ. በ2023 ዓ.ም. በር.ሊ.ጳ. ፍራንቼስኮ ተፈርሞ የወጣው "Fiducia supplicans" የሚለው ሐዋርያው መልእክት ነው። መልእክቱም የተመሳሳይ ፆታ ጥምረት ሕይወት ውስጥ ያሉ ጥንዶች ወደ ካህናት ዘንድ ቀርበው "አባቴ ሆይ! ይባርኩኝ (ይባርኩን)" በማለት ቢጠይቁ ካህናት እንዲባርኩአቸው የሚፈቅድ ወይም የሚያበረታታ ወይም የሚመክር መልእክት ነው። ሆኖም ግን ይህ ሐዋርያዊ መልእክት ብዙ አነጋጋሪ እንደሆነ ቀጥሎአል፤ ብዙ አገራትም በግልጽ ተቃውመውታል፤ ነቅፈውታል፤ ተችተውታል። እንዲያውም አንዳንድ የአፍሪካ ጳጳሳት ጠንከር ባለ መልኩ ምላሽና አስተያየት ሰጥተውበታል፤ ከሰጡትም አስተያየትና ትችት መካከል የተወሰኑትን እንዲህ ይጠቀሳሉ።

በፊት ከአረማዊነት (ከአሕዛብነት) ሕይወት ወደ ክርስትና ጉዞ ይደረግ ነበር፤ አሁን ግን ይህ መልእክት እንደሚያሳየው ከሆነ ከክርስትና ወደ አረማዊነት (አሕዛብነት) እንደመጓዝ ነው።

ምዕራባውያንን ታሳቢ በማድረግ ይህ መልእክት ከተነገረ ጥሩ ነው፤ ግን ደግሞ አፍሪካውያንን ታስቦ ደግሞ ከአንድ ሚስት በላይ የሚፈቅደውን ሕግ ይጽደቅልንና ለሕዝባችን እናስተምር።

ይህ ሐዋርያዊ መልእክት የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የአብሮነት ጉዞ (ሲኖዳሊቲን) አያበረታታም፤ እንዲያውም ኅብረትና አንድነትን የሚቃወም ነው።

በእርግጥ ይህ ሐዋርያዊ መልእክት ስለ ተመሳሳይ ፆታ ጋብቻ አይናገርም፤ ተክሊል ፈጽሙላቸው አይልም፤ ወይም ጋብቻ በአንድ ወንድና ሴት መካከል የሚፈጸመውን ቅዱስ ተግባር መሆኑን የሚሸረሽር አሳብ የለውም። ሆኖም ግን የብዙ አገራት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታን በመጥቀስ እየሞገቱት ይገኛሉ። በመሆኑም ር.ሊ.ጳ. ፍራንቼስኮ በተለያየ ጊዜ ተጨማሪ ማብራሪያ ለመስጠት ተገድደዋል።

ሐዋርያዊ መልእክቱ ስለ ቡራኬ በሚያወራበት ደረጃ እንኳ ይህን ያክል ሙግትና ተቃውም ከተነሣ ስለ ተመሳሳይ ፆታ ጋብቻ ቢወራ በቤተ ክርስቲያን ላይ ምን ሊያስከትል እንደሚችል መረዳቱ አያዳግትም። ሆኖም ግን ሰዎች ይህንን መነሻ በማድረግ በተዛባ መልኩ ስለ ተመሳይ ፆታ ጋብቻ ስለመፈቀዱ በተሳሳተ መልኩ ያወራሉ።

በእርግጥ ሰዎች የሚያወሩትና ይህንን ወሬ በተለያየ መንገድ በመጀመሪያ ስለ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ፣ የቆመችበትና የታነጸችበት መሠረትና የያዘችውን እውነታ ያልተረዱ ናቸው። አንዳንዶች ደግሞ ይህ ነገር የራሳቸውን ምኞትና ፍላጎት ስለሆነ ምኞታቸውን እንዲፈጸም በማለት ብዙዎችን እየቀሰቀሱ የሚያስወሩት ከንቱ ወሬ ነው። ሌሎች ደግሞ ሆን ብለው የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ስምና ክብር ዝቅ ለማድረግና ለማዋረድ የሚሠሩት የውሸት ፕሮፓጋንዳ ነው።

### የማይቀየረው እውነታና የጋብቻ ሕይወት

የተመሳሳይ ፆታ ጋብቻ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለውም፤ እንዲያውም በመጽሐፍ ቅዱስ የተወገዘ ነው(ዘፍ 19)፤ ይህንን የሚያደርጉ ሰዎች በሥጋቸው ቅጣት ይቀበላሉ(ሮሜ 1፡27)፤ የእግዚአብሔር መንግሥት አይወርሱም(1ቆሮ 6፡9-10)።

ሌላው ደግሞ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ለቤተሰብ ሕይወት ትልቅ ክብር አላት፤ ቤተሰብ ደግሞ በቅድስት ቤተሰብ ማለትም በኢየሱስ፣ በማርያምና በዮሴፍ የተመሰለ ነው። በተጨማሪም የቤተሰብ ሕይወት በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን ጥምረትና አንድነት የተመሰለ ነው(ኤፌ 5፡23-31)። ይህ ክቡርና ቅዱስ ምሥጢር ለዘላለሙ ጸንቶ የሚኖር ነው፤ ማንም ስላራገበው ወይም ብዙ የሚዲያ ግርግር ስለፈጠረ የሚለወጥ ነገር አይኖርም። ቤተ ክርስቲያን እውነትን ይዛ ጉዞዋን ትቀጥላለች።

ጋብቻ በወንድና በሴት መካከል የቃል ኪዳን ሕይወት ነው። የወንድና ሴት ቃል ኪዳን የሚደረገውም ከእግዚአብሔር ጋር ነው። እግዚአብሔር የወንድና የሴት ጥምረት (የትዳር ሕይወት) ገና ከፍጥረተ ታሪክ ጀምሮ ባርኮታል(ዘፍ 1፡27)፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ገሊላ ውስጥ ቃና በተባለው መንደር ተገኝቶ ጋብቻን ባርኮታል(ዮሐ 2)። በተጋቡት ወንድና ሴት አማካይነት የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን ፍቅር ይንጸባረቃል፤ ጥንዶቹም የፍቅር ማደሪያ ሆነው ይመሰክራሉ።

ቤተ ክርስቲያን ይህንን ቅዱስ ቃል ታስተምረዋለች፤ ትኖረዋለች። በተጨማሪም በካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ክርስቶስና በሕገ ቀኖና ውስጥ በግልጽና በማያሻማ ሁኔታ አርቅቃ አስፍራዋለች። ስለዚህ የሚቀየር እውነታ የለም፤ ፈጽሞ አይኖርም። ቤተ ክርስቲያን ይህንን እውነታ ይዛ ጉዞዋን እስከ የክርስቶስ ወደዚህች ዓለም ዳግመኛ ተመልሶ መምጣት ድረስ ትቀጥላለች። ሐዋርያው ጳውሎስ "እውነትን በፍቅር እየተናገርን ራስ የሆነውን ክርስቶስ ለመምሰል በሁሉ ነገር እናድጋለን" እንዳለው ሁሉ(ኤፌ 4፡15) ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንም እውነትን በፍቅር እያስተማረች ጉዞዋን ትቀጥላለች።

በአጠቃላይ በካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የሚለወጥ እውነታ የለም፤ ከክርስቶስ የተቀበለችውን እውነታ ትኖረዋለች፤ ለቀጣዩ ትውልድ ምንም ሳይሸራረፍ ታስተላልፈዋለች፤ ሰዎች ይህንን እውነታ መረዳት እንዲችሉ በየጊዜው በተለያየ መንገድ ታስተምራለች።

---

### መልካምን ለመስራት ...

ከገፅ 6 የዞረ

‹ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል›› (ያዕ. 1፡5)። ጌታችን ኢየሱስ ‹‹ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ›› እንዳለው (ሉቃ. 11፡9) ጥበብን ማግኘት የምንችለው አምላካችንን ስንጠይቅ ነው። ጥበብ እንዲህ ትላለች፡ ‹‹እኔ የሚወዱኝን እወድዳለሁ፣ ተግተው የሚሹኝም ያገኙኛል›› (ምሳሌ. 8፡17)።

#### የጥበብ ፍሬዎች

- ጥበብን የሚያገኙ የእግዚአብሔርን ወዳጅነት ያገኛሉ (ጥበ. 7፡14)።
- መልካም ምግባር፣ቁጥብነትንና ጥንቁቅነትን፣ ፍትህንና ጽናትን ታስተምራለች (ጥበ.8፡7)።
- ሰው ያለፈውን እንዲያውቅ፣መጪውንም እንዲተነብይ፣ ምሳሌዎችን እንዲተረጉም፣ እንቆቅልሾችንም እንዲፈታ፣ ምልክቱንና ድንቅ ነገሮችን የዓመታትና የዘመናትንም አመጣጥ እንዲያውቅ ታበቃለች (ጥበ. 8፡8)
- በብልጽግና ጊዜ አማካሪ ናት በችግርና በመከራ ጊዜ ደግሞ አጽናኝ ናት (ጥበ. 8፡9)
- ማመዛዘንና ማስተዋልን ትሰጣለች (ምሳ. 8፡ 5)
- ጥበብ ሲኖረን ክቡርና ቅን ነገርን እንናገራለን፣ ትክክለኛውን ነገር እንለያለን (ምሳ. 8፡6)
- እውነትን እንናገራለን (ምሳ.8፡7)
- ብልጽግናና ክብርን እንጎናጸፋለን (ምሳ. 8፡ 18)
- በመንገዳችን ተማምነን እንሄዳለን፣ እግራችንም አይሰናከልም (ምሳ. 3፡23)
- ስንተኛ የጣፈጠ እንቅልፍ እንተኛለን (ምሳ. 3፡24)
- ድንገት ከሚያስፈራ ነገር ከሚመጣውም ከኃጢአን ጥፋት አንፈራም (ምሳ. 3፡25)
- ጌታ መተማመኛችን ይሆናል (ምሳ. 3፡26)

#### የጥበብ እሴቶች

- ‹‹ጥበብ ከእንቁ ትበልጣለችና የከበረ ነገር ሁሉ አይተካከላትም›› (ምሳ. 8፡11)
- ጥበብ እንዲህ ትላለች ‹‹ፍሬዬ ከወርቅ ይበልጣል›› (ምሳ. 8፡19)
- ‹‹እኔን ያገኘ ሕይወትን ያገኛልና፣ ከጌታም ሞገስን ያገኛልና። እኔን ያጣ ግን ራሱን ይጎዳል፣ የሚጠሉኝ ሁሉ ሞትን ይወድዳሉ›› (ምሳ. 8፡35-36)።

እግዚአብሔርን በእውነተኛ ማንነቱ ስናውቀው እንወደዋለን፣ በቅዱስ ፍርሃት እንፈራዋለን፣ የሚገባውን ክብር እንሰጠዋለን፣ እንታዘዘዋለን፣ በመታዘዛችን ደግሞ በዚህ ምድር ደስታን በሚመጣውም ዓለም ዘላለማዊ ደስታን ይሰጠናል ስለዚህ ይህንን ሁሉ ማድረግ እንድንችል እግዚአብሔር አምላካችን ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች አንዱ የሆነው ጥበብን በመስጠት ይባርከን (1ቆሮ. 12፡8)። አሜን!

#### ዋቢ፡

Antonisamy, Fr. F. ‹‹An Introduction to Christian Spirituality.›› Bombay, St Pauls, 2008.
Stephen, Fr. George S.J. ‹‹Be Fruitful›› Reflections for a Week/Month Retreat. Bombay, St Pauls, 2003.
Wilson, Neil S. ‹‹The Handbook of Bible Application.›› USA, Tyndale house, 2000.

ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት እና ከጤና ክፍል ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

‹‹አትፍሩ፡ ሊፈትናችሁ ኃጢአትንም እንዳትሰሩ እርሱን መፍራት በልባችሁ እንዲሆን እግዚአብሔር መጥቷልና›› (ዘጸ. 20፡20)

### የአዲግራት ሀገረስብከት ...

ከገፅ 1 የዞረ

ሰኔ 21 ቀን 2016 ዓ.ም. የአዲግራት ሀገረስብከት የሥራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት በመገኘት የልምድ ልውውጥ አድርገዋል።
በውይይቱ ከአዲግራት ሀገረስብከት የሐዋርያዊ እና የማህበራዊ ልማት ዘርፍ ኃላፊዎች፣ የአስተዳደር፣ የፋይናንስ፣ የትምህርት፣ የአይቲ እና የአቅም ግንባታ ዘርፍ የተወከሉ 14 ባለሙያዎች የተገኙ ሲሆን ከጠቅላይ ጽ/ቤቱም የማህበራዊ ልማት ኃላፊዎች፣ የአስተዳደር፣ የሰው ኃይል፣ የህፃናት እና የአደጋ ታጋላጭ አዋቂዎች ጥበቃ ቢሮ፣ የፋይናንስ፣ የትምህርት፣ የአይቲ እና የአቅም ግንባታ ዘርፍ ባለሙያዎች ተገኝተዋል።
የአዲግራት ሀገረ ስብከት የማህበራዊ ልማት ዘርፍ የፕሮግራም ኃላፊ የሆኑት አቶ አለም የጉብኝቱን ዓላማ የገለጹ ሲሆን ላለፉት አራት ዓመታት በርካታ ችግሮችን ያሳለፈው ሰበካችንን መልሶ ለማቋቋም እና ለማበረታታት እንደሚያግዝ ገልጸዋል።
በጉብኝታቸውም የቤተክርስቲያን መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ በፋይናንስ እና በሰው ሃይል አስተዳደር እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን የሚያስችሉ አማራጮች ላይ እንደሚያተኩሩ ገልጸዋል።
የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት የማህበራዊ ልማት ዘርፍ ኃላፊ አቶ በቀለ ሞገስ በበኩላቸው ከአዲግራት ለመጡ የሥራ አጋሮች እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት በየዘርፉ የሚገኙ የጠቅላይ ጽ/ቤቱ ባለሙያዎችን በመጋበዝ የልምድ ልውውጡን አስጀምረዋል።
የጠቅላይ ጽ/ቤቱ ባለሙያዎችም የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን የአሥር ዓመት ዕቅድን መሰረት በማድረግ በየሥራ ዘርፋቸው የተከናወኑ፣ በመከናወን ላይ ያሉ እና ወደፊት የታቀዱ አቅጣጫዎች ላይ ለተሳታፊዎች ግብዓት ሰጥተዋል።
በመጨረሻም ከተሳታፊዎች የተነሱ ጥያቄዎች ላይ በመወያየት እና የወደፊት አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ የልምድ ልውውጡ ተጠናቋል።



# የጄን ፌስት ኢትዮጵያ የወጣቶች ፌስቲቫል በሀዋሳ ሀገረስብከት በድምቀት ተከበረ

በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ከሚገኙ የወጣቶች እና የምዕመናን መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች አንዱ የሆነው የፎኮላሬ እንቅስቃሴ አዘጋጅነት የጄን ፌስት ኢትዮጵያ የወጣቶች ፌስቲቫል በሀዋሳ ሀገረስብከት በቅዱስ ልበ ኢየሱስ ቁምስና እና የወጣቶች ማዕከል በድምቀት ተከበረ።
ይህ ዝግጅት በዓለም አቀፍ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን በደቡብ አሜሪካዋ ብራዚል ከተማ እየተከበረ የሚገኝ ሲሆን በኢትዮጵያ ከአራት ሀገረስብከቶች የተሰባሰቡ ከ100 በላይ የሚሆኑ ወጣቶች በአንድነት ሆነው በማክበር ላይ ይገኛሉ። ዝግጅቱ ከሀምሌ 12 እስከ 16/ 2016 የሚቆይ ሲሆን ፌስቲቫሉ የወጣቶች መንፈሳዊ ህንጸት እና የተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎቶችን የያዙ ዝግጅቶች መያዙን የእንቅስቃሴው እና የዝግጅቱ አስተባባሪ ክሪስቲና ከበደ ገልጸዋል።
በዚህ ፌስቲቫል የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ የሐዋርያዊ ክፍል እና የፍትህ እና ሰላም ክፍል ተወካዮች ተገኝተዋል። ክቡር አባ አብነት አበበ የቤተሰብ፣ የምዕመናን እና የወጣቶች ክፍል ሀላፊ በፌስቲቫሉ መክፈቻ ላይ ተገኝተው ለወጣቶች አስተምህሮን አካፍለዋል። በአስተምህሯቸውም ሰለሰላም እና ፍቅር በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ ላይ መሰረት አድርገው አስተምረዋል። አቶ ዘሪሁን አሰፋ ከፍትህ እና ሰላም ክፍል ለፌስቲቫሉ ተሳታፊ ወጣቶች ስለማህበራዊ ትስስር እና የግጭት አፈታት ዘዴዎች ላይ ስልጠናን ሰጥተዋል። ወ/ሪት የምስራች አሰፋ የወጣቶች ክፍል አስተባባሪ የወጣቶች ቢሮ ከሚሰራባቸው አንዱ የህንጸት ዝግጅቶች ውስጥ ወጣቶች የሰላም መሳሪያ መሆን እንዲችሉ የሚያስችላቸውን አስተምህሮዎች እና ዘዴዎች ላይ ስልጠናዎችን እና አስተምህሮዎችን ማዘጋጀት ሲሆን የእንቅስቃሴው አባላት ወጣቶች የዚህ ህንጸት ፕሮግራም ላይ አካል መሆናቸውን ለወጣቶች ገልጸለች። አያይዛም የወጣቶች ቢሮ የሚያደርጋቸውን አገልግሎች አስረድታለች። ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ኤፍሬም የካቶሊክ ዩኒቨርስቲ እና የኮሌጅ ተማሪዎች ሕብረት አስተባባሪ የፕሮላይፍ እንቅስቃሴን በመወከል የካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን መሰረታዊ አስተምህሮ ከሆኑት ውስጥ የሰው ልጅ ሕይወት ከጽንስ እስከ ተፈጥሮአዊ ሞት ድረስ ያለው ክብር ላይ ትምህርትን አስተምራለች።
ዘገባው የኢትዮጲያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ የወጣቶች ቢሮ ነው



# የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት የሐዋርያዊ ሥራዎች መምሪያ ክፍል “የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ትምህርተ ክርስቶስ ለልጆች” በሚል ርዕስ የተዘጋጀ መጽሐፍ አሳትሞ አቀረበ




ተይህ “የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ትምህርተ ክርስቶስ ለልጆች” በሚል ርዕስ የተዘጋጀው መጽሐፍ ልጆች ገና ከለጋ ዕድሜያቸው ጀምረው መሠረታዊ የክርስትና አስተምህሮዎችን በሚገባ አውቀው እንዲያድጉና ስለ እምነታቸው ጥሩ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ ተጠንቶ በጥንቃቄ የተዘጋጀ መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ በውስጡ አስረጂ ታሪኮችንና ምሳሌዎችን እንዲሁም የተለያዩ ገላጭ የሆኑ ሥዕሎችን የያዘ በመሆኑ ልጆች ሳይሰለቻቸው በቀላሉ ማንበብና መረዳት እንዲችሉ ያደርጋል። መጽሐፉ አራት ክፍሎችን የያዘ ሲሆን የእምነት መገለጫ፣ ምስጥራት፣ ሥነ ምግባር እና ጸሎቶችን ይዟል።
በመጀመሪያው ክፍል ሰው ከአፈጣጠሩ ማመን እንዲችል ተደርጎ መዘጋጀቱን ያመለክታል። ሰው የእግዚአብሔርን ፊት ይሻል፤ እግዚአብሔርም ለሰው ልጆች እራሱን ይገልጣል የሚለውን ያብራራልናል። በቀላል መንገድ ስለ እግዚአብሔር እንድናውቅ ፤ እንዴት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር እንደምንችል፤ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ፤ ስለ ክርስቶስ ታሪክ እናም ስለ ቤተክርስቲያን ያስተምረናል።
በሁለተኛው ክፍል ስለ የእግዚአብሔር ጸጋ፤ የምስጥራት ምንነት፤ ለማን እና መቼ እንደሚሰጥ፤ ሚስጥራቱን የመስጠት ኃላፊነት የማን እንደሆነ፤ ምስጥራት የሚሰጡንን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች እንድንረዳ ይረዳናል።
በሶስተኛው ክፍል በእግዚአብሔር መልካም አርአያ የተፈጠረው የሰው ልጅ እንዴት በክርስቶስ ለመኖር መጠራቱን ያሳያል። በሌላ አነጋገር ክርስቲያን የጸጋ ምንጮች ምስጢራት አማካኝነት ያለመቋረጥ እየተለወጠ ክርስቶሳዊና መንፈሳዊ ህይወቱን እንዴት እንደሚመራ ያሳያል። በዋናነትም ስለ አስርቱ ትእዛዛት ምንነትና ከምን እንደሚጠብቁን ማብራርያ ይሰጠናል።
አራተኛው ክፍል ክርስቲያን እምነቱን እንዴት በጸሎት እንደሚመሰክር ያሳያል።በዚሁ መሰረት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙት የጸሎት ሰዎችና ከሕይወታቸው መማር እንደሚቻል ያሳያል።
ይህ መጽሐፍ በክቡር አባ ዳንኤል አሰፋ ተዘጋጅቶ በኢትዮጵያ ካቶሊክ ጳጳሳት ጉባኤ የሐዋርያዊ ሥራዎች ጽ/ቤት አስተባባሪነት የታተመ ሲሆን መጽሐፉን በካቶሊክ መጽሐፍ መደብር ውስጥ ያገኙታል።

ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ከኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የሕፃናት እንክብካቤ እና ጥበቃ ቢሮ ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

**“በመንፈስ ቅዱስ ታትማችኋል” (ኤፌ 2፡13) እያላቸው ነው።**

# የቃሉ ውበት

## “በገነት ካለው ዛፍ ሁሉ ብላ፤ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፥ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና።” (ዘፍጥረት 2፤16-17)

**ኅሊና**፡- እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም ነበር፤ እጅግ መልካም ነበር። ስለተፈጥሮ ውበትና ማራኪነት ታላላቅ የሥነ ጽሑፍ ሰዎች የገጠሙትንና የተናገሩትን መመርመር እንችላለን። እንዲሁም አበቦች፣ ዕፅዋት፣ አዕዋፍ፣ ተራሮች፣ ጅረቶች ... ወዘተ የሚገኙበትን ሥፍራ በመቃኘት የፈጣሪን ድንቅ ሥራ ማስተዋል እንችላለን። የጨረቃን ድምቀት፣ የከዋክብትን ብዛት ስንመለከት፣ ስለማይነገረው **ጥበቡ** ፈጣሪን ለማመስገን እንገደዳለን ።

**ጥበቡ**፡- ታዲያ ክፋት ከየት መጣ? እግዚአብሔር መልካምን ከሰጠ፣ ሰው ደግሞ መጥፎ ነገርን መለሰ ማለት ይሆን?

**ኅሊና**፡- እኔ እንደምረዳው ምድርን ያበጃት ዘንድ ለሰው ኃላፊነትን ተሰጠ። ትልቅ ማዕረግ፣ ትልቅየአገልግሎት ጥሪ፣ በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ለተፈጠረው የሰው ልጅ የተሰጠ ጥሪ፣ የሚያስፈልገውን ሁሉ እያማረጠ መብላት እንደሚችል ተገለጸለት (ዘፍ. 2፤15-16)።

**ሳሙኤል**፡- ግን እኮ፣ መብላት የሌለበትም ዛፍ ነበር፤ አይደል?

**ኅሊና**፡- አዎን፤

**ሳሙኤል**፡- ታዲያ ከሁሉም ዛፍ መብላት ተፈቅዶለታል ማለት አይቻልማ!

**ኅሊና**፡- የተፈቀደውንና የተከለከለውን ማስተያየት የሚያስፈልግ ይመስለኛል። የተፈቀደው ቊጥር ስፍር የለውም። ከዚያ አኳያ የተከለከለው ኢምንት ነው ማለት ይቻላል። ሰው ግን ከተፈቀደው በተከለከለው ላይ ማተኮርን ይመርጣል።

***ሥርጉት***፡- እባቢቱም ወደተከለከለው ትኵረትን መሳብ አይደል የምትፈልገው?

**ኅሊና**፡- ማለትም ወደሚጠቅመው ሳይሆን ወደ ጣጣ ነው የምትስበው ማለት እኮ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ እኮ “ሁሉ ነገር ተፈቅዶልኛል፣ ነገር ግን ሁሉም ነገር አይጠቅምም ይላል (1ኛ ቆሮ. 6፡12)፤

**ጥበቡ**፡- በእርግጥ እሱ ለሐዋርያዊ አገልግሎቱ ሲል፣ ለሌሎች ጥቅም ሲል የተወውን መብትንም ጭምር ይመለከታል። ማለትም የማይጎዳውንም ነገር ጭምር ለሌሎች ጥቅም ሲል መተዉን ለማመልከት ነበር እንዲህ ያለው።

**ሳሙኤል**፡- እኔ ግን አሁንም የተከለከለ ፍሬ ጉዳይ አልገባኝም።

***ሥርጉት***፡- አሁንም በተከለከለው ላይ እያተኮርክ ነው እንዴ?

**ሳሙኤል**፡- ነገሩ እስከተጻፈ ድረስ መጠየቅ አይቻልም እያልሽ እንዳይሆን ብቻ?

**ኅሊና**፡- መጠየቅ በሚገባ ይቻላል። እንዲያውም ይገባል። ባንድ በኩል የተከለከለው ዛፍ የእኛን ውሱንነት ነው የሚያመለክተው። ሰው አምላክ ስላልሆነ ችሎታው፣ መብቱ፣ ነጻነቱ ውሱን ነው። ወሰን ባይኖረውማ ፍጡር ሳይሆን ፈጣሪ ሆነ ማለት ነው። ታዲያ ዛፉ ምሳሌ መሆኑን ልንረሳ አይገባም። ሰው ሆይ ነጻነት እንዳለህ ሁሉ፣ ምንም ያል ቢሰፋ የሆነ ወሰን እንዳለውም አስታውስ ማለት ነው።

**ጥበቡ**፡- ይገርማል፤ በዚህ ምድር ላይ እግዚአብሔር ስለሰጠን ኃላፊነትና ነፃ ፈቃድ አመስግነን እናውቅ ይሆን? በቤተሰብ ውስጥም ሆነ በምንሠራበት ቦታ ሁልጊዜ የሚታየን ሸክም ብቻ ይመስላል። ይህንን ነገር ሳናጣጥብም ሕይወታችንን ስንገፋ ኃዘንተና መሆናችን አይቀሬ ነው።

**ኅሊና**፡- መልካም ነገሮችን ለመፍጠር ማሰብ፣ መትጋትና ወደ ተግባር ማዋል እራሱ መልካም ነግሮችን የፈጠረውን ቲታ ማክበር ይመስለኛል። በዚህ ምድር ላይ ስንኖር ልንደርስባቸው የማንችላቸው ነገሮች እንዳሉ አስበን እናውቅ ይሆን; ፍጡራን እንደመሆናችን መጠን እውቀታችን፣ አቅማችን፣ ችሎታችን ውሱን መሆኑን መገንዘብ ይጠቅመናል ። የተሰጠን ልዩ ማዕረግና ነፃ ፈቃድ ከእግዚአብሔር እንደመጣ ስናውቅ በምስጋና፣ በደስታና በወሮታ እንሞላለን ። ነገር ግን ይህንን ስንክድ ከእውነት ጋር እንጋጫለን ያልሆነውን በመሆን የሌለንን እንዳለን ስናስብ እንታለላለን ።

***ሥርጉት***፡- የተከለከውን ፍሬ መብላት ከትዕቢት ጋር ይገናኛል ማለት ነው?

**ሳሙኤል**፡- እኔ ግንኙነቱ አይታየኝም። ይልቁንም ዋናው ፈተና መጎምጀታቸው አይደለም እንዴ?

***ሥርጉት***፡- መጎምጀትና ትዕቢት ፈጽሞ አይገናኙም እያልክ ይመስለኛል።

**ጥበቡ**፡- በሌላ አጋጣሚ ወይንም ሁሌ አይገናኙ ይሆናል። እዚህ ላይ ግን የሚገናኙ ይመስለኛል።

**ኅሊና**፡- እኔም በዚህ ታሪክ ውስጥ የትዕቢት ጉዳይ ይታየኛል። ትዕቢትም ማለት የማናውቀውን ወይም ልናውቅ የማንችለውን ለመጨበጥ መፈለግ፣ ወይም ጨብጫለሁ ማለት፤ አቅማችን የማይፈቅደውን አደርጋለሁ ማለት ይመስለኛል። ውብ አድርጎ ለሠራንና መልካሙን ለሰጠን አምላክ ወሮታን አለመመለስ ። እሱ የሚለንን ከማመን ፈንታ ማመጽና የርሱ ተቀናቃኞች ለመሆን መፈለግ። ሰው መሆናችን ከቶ የማይካድ ሆኖ ሳለ እንደ ፈጣሪ ለመሆን መፍጨርጨር ትዕቢት ይመስለኛል።

**ጥበቡ**፡- አዳምና ሔዋንም እኮ ይህንን ነው ያደረጉት! በግሩም ሁኔታ ከሚንከባከባቸው ከፈጣሪያቸው ቃል ይልቅ የተንኮለኛይቱን እባብ አስተያየት ተቀብሉና አመኑ ። “ክፉና ደጉን ዛፍ መብላት ሞት ያመጣል” ከሚለው የእግዚአብሔር ቃል ይልቅ፣ “እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ” የሚለውን የእባቢቱን ቃል አመኑ።

**ኅሊና**፡- ገና ከመነሻው የእባቢቱ አስተያየት ሐሰት የሞላበት ነበር ። ለመግቢያ የተጠቀመችው የእግዚአብሔርን ቃል በማጣመም ነበር ። “በውኑ ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ እግዚአብሔር አዟችኋልን” አለች።

***ሥርጉት***፡- እንዴ! ብሉ እንጂ አትብሉ ብሎ መቼ ጀመረ!

**ኅሊና**፡- የተጣመመ ትርጉም ነዋ? መልእክቱን በማጣመም ወዳልተፈለግ መንገድ ለመውሰድ የተጠቀምችበት ዘዴ ወይንም ተንኮል እኮ ነው።

**ጥበቡ**፡- አዎን፣ ረጋ ብለን ካላሰብነው እኮ መልእክቱ መጣመሙን ላናስተውል እንችላለን። እግዚአብሔር ግን ስለተከለከለ ዛፍ ተናገረ እንጂ በገነት ውስጥ ያለውን ፍሬ እንዳትበሉ አላላቸውም ። ይልቁንም ለምግብነት የሚያስፈልጋቸውን ብሉ ነው ያላቸው (ዘፍ. 2፡16)።

**ኅሊና**፡- እዚህ ላይ አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር መታመንን ረሱ። ይቁንም በተጠመዘዘው፣ ከመስመር በተንሸራተተው ጉዳይ ተማረኩ። በመሠረቱ ክፉና ደጉን የሚያሳውቀው ዛፍ ሁሉን ነገር የማወቅ ምሳሌ ሊሆን ይችላል ። ለምሳሌ እግዚአብሔር ክፉና ደጉን ያውቃል ሲባል እግዚአብሔር ሁሉን ያውቃል ለማለት ነው። ክፉውንም ደጉንም አንድም ሳይቀር ሁሉንም ያውቃል ። ሁሉንም ማወቅና መቆጣጠር የእግዚአብሔር እንጂ የሰው አይደለም ። እንግዲህ ችግሩ እዚህ ላይ ነው ። ሰው እንደ እግዚአብሔር ሁሉን መቆጣጠር፣ መረዳት አለብኝ ሲል ያንን ክፉንና ደጉን የሚያሳውቀውን፣ የተከለከለውን ዛፍ ፍሬ በላ ማለት ነው።

**ጥበቡ**፡-ስለዚህ የእግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ ይህ ነበር ለማለት ይቻላላ?!

**ኅሊና**፡- “ከዚህ ፍሬ አትብላ፣ በበላህ ጊዜ ከባሕርይህ ጋር የሚጋጭ ነገር ታደርጋለህ፣ ወደ ሞት ይወስድሀል” ሲል ይህ የፍቅር ማስጠንቀቂያ ነበር። ልክ “ልጄ ሆይ ወደዚህ አካባቢ ከመሸ ወዲህ ለብቻህ አትሂድ አደገኛ ነው። ማጅራት መቺዎተ አሉ” እንደሚሉ ወላጆች። ልጃቸውን ነፃነት መንፈግ ፈልገው ሳይሆን ለልጃቸው ዋስትና ሲሉ። ልጅ “የወላጆቹ ማስጠንቀቂያ ትክክል ነው፣ እቀበለዋለሁ” ካለ ለአደጋ እንደማይጋለጥ የታወቀ ነው። “እኔ ትልቅ፣ እንዳልዝናና ሊከለክሉኝ ነው ይህንን የሚሉት” በማለት የሚያመሽና ወደዚያ አካባቢ የሚመላለስ ከሆነ ግን ለአደጋ ሊጋለጥ ይችላል።

***ሥርጉት***፡- እግዚአብሔር ከዚህ ፍሬ አትብሉ ያለው ለጥቅማቸው አስቦ ነው ማለት ነዋ!

**ጥበቡ**፡- ነገር ግን ይህንን ቸል ብለው፣ የእባቡን ምክር ሰምተው በሉ። ለአደጋ ተጋለጡ፣ ጸጋን ተገፈፉ ደነገጡ፣ ተራቆቱ፣ ሸሹ።

**ኅሊና**፡- እባቡ በማራኪ ንግግር እንዳሳመናቸው “እንደ እግዚአብሔር” ሆነው ቢሆን ኖሮ ባልደነገጡ፣ ባልተራቆቱ ባልሸሹ ነበር። እግዚአብሔር እኮ አይደነግጥም፣ አይሸሽም፣ አይፈራም፣ አይደበቅም።

**ሳሙኤል**፡- አሁን ግልጽ እየሆነልኝ መጣ።

**ኅሊና**፡- ከታሪኩ እንደምንረዳው ይህ ሁሉ የተከሰተው ገና እግዚአብሔር ሳያገኛቸው በፊት ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ወደነሱ በመጣበት ሰዓት አንዱ ሌላውን መክሰስ ጀመረ።

***ሥርጉት***፡- መደንገጥና መሸሽ ብቻ ሳይሆን ሌላም ጣጣ መጣ ማለት ይሆን?

**ኅሊና**፡- ትክክል በልሻል። ከፈጣሪ ጋር ያለው ግንኙት ሲበላሽ እርስ በእርስ ያለውም ግንኙነት ይበላሻል። የአምላክ ትእዛዝ ከተጣሰ በኋላ በወንዱና በሴቲቱ መሀል የነበረው ግንኙነት ተናጋ። ረዳቱ እንድትሆነው ነበር እንጂ እንዲካሰሱ አልነበረም የተፈጠረችው “ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም” (ዘፍ. 2፡18) በማለት ነበር እግዚአብሔር ሔዋንን የፈጠራት። “ሁለቱ አንድ ሥጋ ይሆናሉ” (ዘፍ. 2፡24) በማለትም የጌታን ክቡርነት፣ የትዳርን ትልቅነት፣ የተክሊልን ጥብቀት ገለጸ።

**ሳሙኤል**፡- እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ አለኝ፤ ብቻ ወደ ሌላ ርእስ ሄድክ እንዳትሉኝ።

**ጥበቡ**፡- ምንድነው ተናገር።

**ሳሙኤል**፡- ሴት ለአዳም ረዳት እንድትሆን ተፈጠረች ማለት ከወንድ ታንሳለች ማለት አይደለም እንዴ? ታዲያ ችግር አያመጣም? በተለይም በዛሬ ጊዜ?

**ኅሊና**፡- ይኸውልህ፤ በዘፍጥረት 1፡26-27 እንደተገለጸው ሁለቱም በአምላክ መልክና ምሳሌ ስለተፈጠሩ እኩል ማዕረግና ክብር አላቸው። ለነገሩ “ረዳት” የሚለው ቃል ዝቅተኛነትን አያመለክትም። ቢያመለክትማ ኖሮ “እግዚአብሔር ረዳቴ ነው” የሚለውን የመዝሙረ ዳዊት አባባል እንዴት ልንተረጉመው ነው። መቼም መዝሙሩ “እግዚአብሔር ረዳቴ ነው” ስል ከኔ በታች ነው ማለት እንዳልሆነ ለሁላችን ግልጽ ነው (መዝ. 63፡7)

***ሥርጉት***፡- አሁን ውደ ቅጣቱ ብንመለስ ጥሩ ይመስለኛል። ለየት ያለ የምንማረው ነገር ይኖር ይሆን?

**ጥበቡ**፡- እንደኔ ቅጣቱ ከተጠበቀው ያነሰ ሆኖ እናገኘዋለን። አዳምና ሔዋን በወቅቱ አልሞቱም። ከገነት እንዲወጡ ቢደረግም እንኳን እግዚአብሔር ልብስ እንዳለበሳቸው እናነባለን። ቅጣታቸውን ከማቅለልም በተጨማሪ ጌታ አምላክ ልብስ ይሰጣቸዋል። ጌታ አምላክ ከብርድና ከውርደት ይጠብቃቸዋል።

በክቡር አባ ዳንኤል አሰፋ (ዶ/ር)

ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት የሴቶችና ቤተሰብ ጉዳይ ክፍል ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

**“ለምትዋጁበት ቀን ማረጋገጫ እንዲሆናችሁ የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ” (ኤፌ. 4፡30)**

# የብፁዕ አቡነ ዶሚኒኮ ክረሽንቲኖ ማሪኖዚ አጭር የሕይወት ታሪክ



ብፁዕ አቡነ ዶሚኒኮ ማሪኖዚ ሰራልታ በምትባል መንደር በሳን ሰቨሪኖ ደለ ማርኬ ከተማ ከአባታቸው ራፋኤሌ ማሪኖዚና ከእናታቸው ዶመኒካ አንቶኒኒ እ.ኤ.አ. ኅዳር 21 ቀን1926 ዓ. ም. ተወለዱ። በዚህ ጽሁፍ የተጠቀሱ አቆጣጠሮች በሙሉ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር መሆናቸውን ለመግለጽ እወዳለሁ።

አቡነ ዶሚኒኮ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ዘርዓ ምንኩስናው ገብተው፤ በነሐሴ 30 ቀን 1944 ዓ.ም. የካፑቺን ማኅበር አባል የሚያደርጋቸውን የመጀመሪያ የምንኩስና መሀላ ፈጸሙ። ከዚያም እ.ኤ.አ. ኅዳር 23 ቀን 1947 ዓ.ም. የመጨረሻ መሀላቸውን ከፈጸሙ በኋላ በ24 ዕድሜያቸው እ.ኤ.አ. ታህሣሥ 17 ቀን1950 ዓ.ም. ማዕረገ ክህነት ተቀበሉ።

የክህነት ማዕረግ እንደተቀበሉ ከ1950-1955 ድረስ በምዕራብ ስዊዘርላንድ በሚገኘው በታዋቂው ፍራይቡርግ ዩኒቨርሲቲ ተምረው በፍልስፍና በዶክተሬት ተመረቁ። ከ1955 እስከ 1958 ድረስ በሎረቶ በቲዎሎጂ ተቋም የቤተክርስቲያን ታሪክ መምህር ሆነው አገለገሉ። ቀጥሎም ከ1959 እስከ 1969 ድረስ በአንኮና ከተማ የፍልስፍና መምህርና የተማሪዎች አለቃ ሆነው አገለገሉ።

ብፁዕ አቡነ ዶሚኒኮ ማሪኖዚ እ.ኤ.አ በሐምሌ 1968 ዓ.ም. ለጉብኘት ወደ ኢትዮጵያ መጡ። ከዚያም ቀጥሎ እ.ኤ.አ ኅዳር 17 ቀን 1972 ዓ/ም በቫቲካን የሚገኘው የስብከተ ወንጌል ቢሮ የመጀመሪያው የሆሣዕና ሀገረ ስብከት አስተዳዳሪ (Apostolic Administrator of the Prefecture) አድርገው ሾሟቸው (ሆሣዕና ሀገረ ስብከት መጀመሪያ የተቋቋመው የካቲት 13 ቀን1940 ዓ.ም. ነበር፤ ከዚያም የሀረር ሀገረ ስብከት አካል ሆኖ ቆየ)። ጥር 1ቀን1973 ዓ.ም. አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ ጥር 12 ቀን 1973 ዓ.ም. ቅዱስ አንጦንዮስ ቤተክርስቲያን አሸራ በመግባት ሐዋርያዊ አስተዳዳሪነት ሥራ ጀሩ። ከዚያም ወደ ሶዶ ከተማ በመዛወር የራሳቸው መኖሪያ በ1977 ዓ.ም. ተጀምሮ በ1978 ዓ.ም. እስኪጠናቀቅ ድረስ ቆንቶ በሚገኘው ካፑቺን ታናናሽ ወንድሞች ገዳም ተቀመጡ። እ.ኤ.አ. ታህሣሥ 30 ቀን 1977 ዓ.ም. የሆሣዕና ሐዋርያዊ አስተዳደር ተብሎ ሲጠራ የነበረው ሶዶ-ሆሣዕና ሐዋርያዊ አስተዳደር ተብሎ እንዲጠራ ተወሰነ። መቀመጫውም ሶዶ ከተማ እንዲሆን የካቲት 23 ቀን 1979 ዓ.ም. ተወሰነ። ጥቅምት15 ቀን 1982 ዩኩንዲያና (Iucundiana) በሚል መጠሪያ ስም ጳጳስ እንዲሆኑ ተሹመው፤ በታህሣሥ 10/1982 ዓ.ም. በሎረቶ ባዚሊካ የመጀመሪያ የሶዶ ሆሣዕና ሀገረ ስብከት ጳጳስ ሆነው ተቀቡ። በ1994 ዓ.ም. የሶዶ ካቴድራል ቤተክርስቲያን አሠርተው አስመረቁ። እ.ኤ.አ. ጥር 5 ቀን 2007 ዓ.ም. በጡረታ ተገለሉ። እርሳቸው በጡረታ ከተገለሉ በኋላ ሶዶ ሆሣዕና ሀገረ ስብከት ተብሎ ይጠራ የነበረው በሁለት ሲከፈል እ.ኤ.አ. ጥር 20 ቀን 2010 ብፁዕ አቡነ ወልደጊዮርጊስ ማቴዎስና ብፁዕ አቡነ ሮድሪጎ ሜህያ ሳልዳሪያጋ የሆሣዕናና የሶዶ ሀገረ ስብከቶች ጳጳሳት ሆነው ተሾሙ።

ብጹዕ አቡነ ዶሚኒኮ በጡረታ እስከተገለሉበት ጊዜ ድረስ ከፍተኛ ሐዋርያዊና የልማት አገልግሎቶችን ያበረከቱ የወንጌል አርበኛ ነበሩ።

ስለ አቡነ ዶሚኒኮ ማሪኖዚ አገልግሎትና ሕይወት ተነግሮ አያበቃም። ሁሉም ሰው አንድን ትልቅ ሰው ቤተክርስቲያን እንዳጣች ይስማሙበታል። የወንጌል ተልእኮ ሁለት ገጽታ አለው ይሉ ነበር። አንደኛው መንፈሳዊ አገልግሎት ሲሆን ይህ ውጤቱን ለመለካት የሚያስቸግር የማይታይ ገጽታ ያለው ሲሆን የምእመናን በእምነት ማደግን ያመለክታል፤ ሌላኛው ገጽታ ደግሞ የሚታይ ገጽታ ያለው ሲሆን ይኸውም በፍቅር ሥራ ወይም በልማት የሚካተት ነው ይሉ ነበር። እርሳቸው ያገለገሉባቸው የሶዶና ሆሣዕና ሀገረ ስብከቶች በመንፈስም ሆነ በፍቅር ሥራ አድገዋል። እርሳቸው ሐዋርያዊ ተልዕኮ ሲጀምሩ ያሁኑ ሶዶ ሆሣዕና ሀገረ ስብከቶች ምእመናን ብዛት በግምት በአሥራ አንድ ቁምስናዎች ወደ 21,000 የሚጠጋ ሲሆን ባሁን ጊዜ ግን የምእመናን ቁጥር አብበው ቁምስናዎች በርክተው በግምት ከ350,000 በላይ ምእመናን ያለባቸው ቁምስናዎች አፍርተዋል። ስለዚህ ሁሉ እግዚአብሔርን ማመስገን ይገባናል።

አቡነ ዶሚኒኮ ማሪኖዚ ለሁለንተናው ለሰው ልጆች እድገት ያበረከቱት አስተዋጽኦ እጅግ ከፍተኛ ነበር። የቁምስናዎች ቁጥርና የምእመናን ቁጥር መጨመሩ የእርሳቸው ጥረት ፍሬ ነው። የካቴክስቶች ማሰልጠኛዎችን በማቋቋምና ካቴክስቶችን በማሰልጠን ብቁ ካቴክስቶችን ለአገሪቱ አፍርተዋል። መምህራን ቀጣይ ሥልጠና እንዲያገኙ በማድረግ የመምህራን የማስተማር ግንዛቤ ከፍ እንዲል አተዋጽኦ አበርክተዋል። ዘርአክህነት ትምህርት ቤቶችን በሆሣዕናና በአዲስ አበባ በመመሥረት በርካታ ካህናትን ለሀገረ ስብከቶች አፍርተዋል። እርሳቸው በሠሩባቸው ሀገረ ስብከቶች (ሶዶና ሆሣዕና) የወጡ በርካታ ካህናትና ደናግል በመላው ዓለም ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን እያገለገሉ ይገኛሉ። ትምህርት ቤቶችንና የጤና ጣቢያዎችን አስፋፍተዋል። እርሳቸው ያቋቋሙት የዱቦ ሆስፒታል ትውስታ እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ ከእርሳቸው አልተለየችም ነበር። ላገኙት ሰው ሁሉ የዱቦ ሆስፒታል እንዴት ነች? ብለው ሳይጠይቁ አያልፉም ነበር። የሴቶች ሙያ ማሠልጠኛዎችን አቋቁመዋል። የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ በቆንቶ/ሶዶ እንዲቋቋም መሣሪያ ነበሩ። ብሩህ ተስፋ በመባል የሚታወቀው መዋዕለ ሕፃናት ማሰልጠኛ በፍቅር ድናግል ማኅበር በሶዶ ከተማ እንዲመሠርት የጋበዙ እርሳቸው ነበሩ። ከካፑቺን አባቶች ጋር በመተባበር ንጹህ ውሀ በሌለባቸው አከባቢዎች ንጹህ ውሃ ተደራሽ እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል። የገጠር መንገዶችና ድልድዮች በመገንባት ለሕዝብ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲመቻች አስተዋጽኦ አድርገዋል።

አገልግሎታቸውን ካበቁ በኋላ በ2010 ዓ. ም. ወደ ጣሊያን አገር ከተለመለሱ በኋላ ለብዙ ዓመታት ኑዛዜ በማናዘዝ ለነፍሳት መዳን በሎረቶ ባዚሊካ ከፍተኛ አገልግሎት ሲያበረክቱ ቆይተዋል። ከሦስት ዓመት በፊት ወደ ማቸራታ ገዳም ተዛውረው ምንም ሳያጉረመርሙ ለሁሉ ሰው አርአያ በሚሆን ሁኔታ የሽምግልና ሕይወት አሳለፉ። ከማረፊቸው ሁለት ሣምንት አስቀድሞ የኢትዮጵያ ጳጳሳት ጉባኤ አባላት በሙሉ ወደ ማቸራታ ገዳም በመሄድ በአካል አግኝቷቸው ጸሎት አድርገው ከተሰናበቱ በኋላ፤ በሐምሌ 19 ቀን 2024 ዓ. ም. በ98 ዕድሜያቸው፤ በ80 ዓመት የምንኩስና ዓመታቸው፤ በ74 የክህነት አገልግሎትና በ42 የጵጵስና አገልግሎት በኋላ፤ የሶዶ ሀገረ ስብከት አዲስ ጳጳስ በተሾሙ ልክ በአንድ ወር ጊዜ በጣሊያን አገር በማቸራታ ካፑቺን ገዳም ከምድራዊ ድካም አረፉ። የፍታት ጸሎት ባገለገሉበት በሎረቶ ማርያም ባዚሊካ ሦስት ጳጳሳትና ከሃምሳ የሚበልጡ ካህናትና በርከታ ምዕመናን በተገኙበት ከተከናወነ በኋላ የቀብር ሥነ ሥርዓታቸው በማቸራታ ገዳም መቃብር ተከናውኗል።

በኢትዮጵያ የጳጳሳት ጉባኤ ረዳት ሰብሳቢ ሆነው አገልግለዋል። አቡነ ዶሚኒኮ ማሪኖዚ ያለ ምንም ማጋነን በኢትዮጵያ ካገለገሉ እንደ አቡነ ያዕቆብ፤ እንደ ካርዲናል ማሳያ፤ እንደ አባ ፓስካል ዴ ሉሾን እንደ አቡነ ጋስፓሪኒ ትልቅ ሚሲዮናዊ ነበሩ። የቅድስና ሕይወት የኖሩ፤ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት መስፋፋት ከፍተኛ ተጋደሎ ያበረከቱ ቅዱስ አባት ነበሩ። አቡነ ዶሞኒኮ ማሪኖዚ መንፈሳዊ አባት፤ በጣም አዋቂ ሰው፤ ትሁት፤ አዝናኝ፤ ለጋስ፤ ሰውን አክባሪና አፍቃሪ፤ ጸሎተኛ፤ የካፑቺን ሕይወት አርአያ፤ በአጠቃይ ቅዱስ ሰው ነበሩ። በአገልግሎት ዘመናቸው እያንንዱን ቁምስና በዓመት አንድ ጊዜ ይገበኙ ነበር። ለምእመናን፤ ለካቴክስቶች፤ ለመነኮሳትና ለካህናት አባታዊ ፍቅር ነበራቸው። ነፍሳቸውን አምላክ በአብርሃም በይስሀቅ አጠገብ በመንግሥቱ ያሳርፍልን። በእርሳቸው ዕረፍት ላዘኑ ሁሉ በተለይም ለሶዶና ለሆሣዕና ሀገረ ስብከቶችና ለካፑቺን ማኅበር አባላት አምላክ መጽናናትን ይላክላቸው።

*አባ ኃይለገብርኤል መለቁ*

## ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ ...

ከገፅ 1 የዞረ

ክቡር አባ ጌታሁን ፋንታ እ.ኤ.አ የካቲት 25 ቀን 1973 ዓ.ም. በነቀምት ሀገረስብከት ምዕራብ ወለጋ አለኩ ቃቄ የተወለዱ ሲሆን በቅዱስ ፍራንቼስኮስ ነገረ መለኮት ትምህርት ቤት የፍልስፍና እና የነገረ መለኮት ማዕከል የክህነት ትምህርት ዝግጅታቸውን በመጨረስ እ.ኤ.አ ሀምሌ 1 ቀን 2001 ዓ.ም ክህነት ተቀብተዋል። በአሜሪካ ቺካጎ በሚገኘው የደፓል ዩኒቨርስቲ በሰው ሃይል አስተዳደር የማስተርስ ዲግሪያቸውን ተቀብለዋል።

ክቡር አባ ጌታሁን ፋንታ በሰኮ የመድኃኔዓለም ቁምስና እና መቲቻ የቅድስት ማርያም ቁምስና ቆሞስ በመሆን ያገለገሉ ሲሆን ለቬንሰንሽያን ገዳም የሴሚናሪዎች አለቃ፣ በሁለት የኃላፊነት እርከን እና ወቅት የቬንሰንሽያን ገዳም የበላይ አለቃ በመሆን አገልግለዋል።

ክቡር አባ ጌታሁን በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት 100ኛ ዓመቱን በማክበር ላይ የሚገኘው የላዛሪስት ካቶሊክ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር እና የፍቅር ሥራ ልጆች ማህበር መንፈሳዊ ኃላፊ በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ።

የኢትዮጵያ ካቶሊክ ጳጳሳት ጉባኤ ደስታውን እየገለጸ ለክቡር አባ ጌታሁን ፋንታ የተባረከ የአገልግሎት ዘመን እንዲሆንላቸው ይመኛል።

## የክቡር አባ ኃይሌ ሚካኤል ...

ከገፅ 1 የዞረ

በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የሶዶ ሀገረስብከት ጳጳስ የነበሩት የብፁዕ አቡነ ጰጋዬን የጡረታ ስንብት ተከትሎ ብፁዕ አቡነ ስዩም የሆሳዕና ሀገረስብከት ጳጳስ በጊዜያዊነት ሰበካውን ሲመሩ የቆዩ ሲሆን ባሳለፍነው ወር ለሶዶ ሀገረስብከት ክቡር አባ ደጀኔ ቋሚ ጳጳስ ሆነው በርዕሰ ሊቃነጳጳሳት ፍራንቸስኮስ መሾማቸው ይታወቃል።

ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነየሱስ የአዲስ አበባ ሀገረስብከት ሊቀ ጳጳስ እና የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ጳጳሳት ጉባኤ ፕሬዝደንት የሲመተ ጵጵስና ስርዓቱን የሚመሩ ሲሆን ብጹዕ አቡነ ስዩም እና ብፁዕ አቡነ አንጀሎ ፓጋኖ ከብፁዕነታቸው ጋር ስርዓቱን እንደሚመሩ ተገልጿል። በመስዋዕተ ቅዳሴው ሁሉም የኢትዮጵያ ጳጳሳት፣ ካህናት፣ ገዳማውያን እና ምዕመናን ይገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል።

እ.ኤ.አ. መጋቢት 21 ቀን 1972 በኢትዮጵያ ወላይታ ክፍለሀገር የተወለዱት የካፑቺን ቅዱስ ፍራንቼስኮስ ታናናሽ ወንድሞች ካህን ክቡር አባ ደጀኔ በአሁኑ ጊዜ የሶዶ ሀገረስብከት የሐዋርያዊ ሥራዎች አስተባባሪ ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ። የክህነት ጉዟቸው የጀመረው በቦዲቲ አንደኛ ደረጃ እና ጁኒየር 2ኛ ደረጃ ት/ቤት፣ በመቀጠልም ቦዲቲ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣ እና በ2000 የፍልስፍና እና የነገረ መለኮት ጥናቶችን ካጠናቀቁ በኋላ በክህነት ሹመት ተቀብለዋል።

የክቡር አባ ኃይሌ ሚካኤል (ደጀኔ) ሂዶቶ በተለያዩ የቤተክርስቲያን ኃላፊነቶች ያገለገሉ ሲሆን ከእነዚህም መካከል የቁምስና ቆሞስ፣ የገዳሙ ማኅበራዊ ጉዳይ ኃላፊ፣ እና የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋም ዳይሬክተር ከብዙዎች በጥቂት ይገለጻሉ። ክቡር አባ ኃይሌ ሚካኤል (ደጀኔ) ሂዶቶ በትምህርት ዝግጅታቸው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሶሺዮሎጂ እና በማህበራዊ አንትሮፖሎጂ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን እና በኦታዋ ካናዳ ከሚገኘው የቅዱስ ጳውሎስ ዩኒቨርሲቲ በማህበረሰብ ስነ-ምግባር ማስተርስ አግኝተዋል።

ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት የሴቶችና ቤተሰብ ጉዳይ ክፍል ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

**‹‹ ነፍሴ ሆይ፥ ለምን ታዝኛለሽ? ለምንስ ታውኪኛለሽ? የፊቴን መድኃኒት አምላኬን አመሰግነው ዘንድ በእግዚአብሔር ታመኚ›› (መዝ 43፡5)**

# የ ጥ ሪ ማዕ ድ

## የጸሎት ሐዋርያነት



<u>**ነሐሴ**</u>

<u>*ለፖለቲካ መሪዎች*</u>

የፖለቲካ መሪዎች ህዝባቸውን እንዲያገለግሉ፣ ሁሉንም ባቀፈ መልኩ እና ለጋራ ሰብዓዊ ተጠቃሚነት እንዲሰሩ፣ ስራ ያጡትን እንዲንከባከቡ እና ለድሆች ቅድሚያ እንዲሰጡ እንፀልይ።

<u>**AUGUST**</u>

<u>***FOR POLITICAL LEADERS***</u>

**Let us pray that political leaders be at the service of their own people, working for integral human development and the common good, taking caring of those who have lost their jobs and giving priority to the poor.**

<u>**የማቅረቢያ ጸሎት**</u>

ኢየሱስ ሆይ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ንፁህ ልብ አማካይነት የዚህን ቀን ጸሎቴን ፣ሥራዬን፣ ደስታዬን፣ ሐዘኔንና ሥቃዬን በመላው ዓለም ከሚቀደሰው ቅዳሴ ጋር አንድ አድርጌ ለአንተና ለቅዱስ ልብህ ሐሳቦች አቀርባለሁ፤ ለነፍሳት ደኅንነት፣ ለኃጢአት ካሣና ለክርስቲያኖች አንድነት፣ ለጳጳሳትና ለጸሎት ሐዋርያነት ማኅበር በተለይም ለዚህ ወር በርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ለተሰጡት ሐሳቦች አቀርባለሁ።





## ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ በኢትዮጵያ የመሬት መንሸራተት ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ጸሎት አደረጉ

ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ ሐምሌ 21 ቀን 2016 ዓ.ም. የገብርኤል ብስራት ባደረሱት ጸሎት በኢትዮጵያ በደረሰው የመሬት መንሸራተት አደጋ ለተጎዱ ሰዎች ጸሎት አደረጉ።
ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ በትላንትናው የገብርኤል ብስራት ጸሎት ማጠቃለያ ላይ ባደረጉት ንግግር በደቡብ ኢትዮጵያ ጎፋ ዞን መንደር ውስጥ በደረሰው ከፍተኛ የመሬት መንሸራተት አደጋ ለተጎዱ ወገኖች ጸሎታቸውን አድርሰዋል።
ቅዱስነታቸው በአደጋው እርዳታ ለሚሰጡ የነፍስ አድን ሰራተኞች በቅርበት በጸሎት እንደሚያግዙ ገልጸዋል። በደቡብ ኢትዮጵያ በጎፋ ዞን በተከሰተው ከባድ የመሬት መንሸራተት የ257 ሰዎችን ህይወት የቀጠፈ ሲሆን የተጎጂዎች ሞት አሁንም እየጨመረ ሲሆን አደጋውም አፋጣኝ ሰብዓዊ እርዳታ ያስፈልገዋል ብለዋል።


**Pope Francis prayers for victims of the landslides in Ethiopia, lamenting that while calamities and hunger continue worldwide, the manufacture and sale of weapons fuel wars and human suffering.**

***Ethiopian Church on frontline of relief efforts in mudslide area***

Speaking at the conclusion of the Sunday Angelus, Pope Francis offered his prayers for the victims of the large landslide that swept through a village in southern Ethiopia. He said he is close to the suffering people and to those rescue workers providing assistance. The death toll of 257 victims continues to rise following the two devastating landslides in Gofa Zone, Southern Ethiopia, while the population affected is in desperate need of humanitarian aid. The first landslide in the remote mountainous locality of Kencho Shacha Gozdi was triggered by heavy rains on 21 and 22 July, and the second engulfed those who had gathered to rescue people.

*Vatican News*

## ተክሊል በአግባቡ እንዲፈጽሙ ቤተክርሰቲያን ታበረታታለች



ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ጋብቻ በአንድ ካቶሊካዊ ወንድና አንዲት ካቶሊካዊት ሴት መካከል ብቻ ልዩ ዝግጅት ተደርጎ ይፈጸማል። ይሁን እንጂ ያለው ገሃዳዊ እውነታ ብዙ ካቶሊካውያን በፍቅር ምክንያት ከሌሎች እምነት ተከታዮች ጋር ጋብቻ ፈጽመው መኖራቸው መልካም ሆኖ በዚሁ ምክንያት ከሚወዱት ቅዱስ ቁርባን ርቀው በምኞት ብቻ እንዲኖሩ አድርጓቸዋል። ይህ ጉዳይ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን አባቶች በትዳር ምክንያት ከቅዱስ ቁርባን ርቀው ያሉ ነፍሳት ጉዳይ አሳሳቢ መሆኑን በመረዳትና ለሦስት ዓመታት (እ.አ.አ 1962-1965) ውይይትና ምክክር ከተደረገበት በኋላ ካቶሊካውን ምእመናን ከሌሎች እምነት ተከታዮች ጋር በጋብቻ መኖር እንዲችሉ በልዩ ሁኔታ ቤተክርስቲያን ቅድመ ሁኔታ አስቀምጣ ተክሊሉ እንዲፈጸም መመሪያ አጽድቃለች። ይኸውም ካቶሊካዊ ቅልቅል ጋብቻ(Mixed Marriage) እ.አ.አ 1965 ዓ.ም ጀምሮ በካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ተግባራዊ ተደርጓል፡ (የካቶ/ቤ/ሕግ ቀኖና 1125) ተመልከቱ ። ይህ ዓይነቱ ጋብቻ ሲፈጸም መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎቹ ።

1. ካቶሊክ የሆነው ወገን በዚህ ጋብቻ ምክንያት ከካቶሊክ ሃይማኖት ወደ ኋላ የሚያስቀረውን ማንኛውንም አደጋም ይሁን እንቅፋት እንደሚያሸንፍ ቃል ሲገባ
2. 2. ካቶሊክ የሆነው ወገን ከዚህ ጋብቻ የሚገኙት ልጆች በካቶሊክ ሃይማኖት እንዲጠመቁና እንዲያድጉ ቃል ሲገባ
3. ካቶሊክ ያልሆነው ወገን ካቶሊክ የሆነውን ወገን ስለገባው ቃልና ስለሚኖርበት ግዴታ በቂ መረጃና ግንዛቤ ማግኘትና መፈረም ይኖርበታል
4. ሁለቱም ተጋቢዎች በሚመለከታቸው በጋብቻ ዋና ዋና ጉዳዮች በቤተክርስቲያን አገልጋዮች ግንዛቤ አግኝተው ለመኖር መስማማትና ጋብቻው ሊፈርስ የማይችል ጋብቻ መሆኑን ተረድተው ለመኖር በቤተክርስቲያን የቅልቅል ጋብቻ መዝገብ ላይ በጳጳስ ፈቃድ (Dispensation )ወደ ቤተክርስቲያን ቀርበው ከፈረሙ በኋላ መሆኑን ህገ ቀኖና ያዛል (ቀኖና 1108፣1086 ፣1125፣1127 ተመልከት። ይህ ዓይነቱ ጋብቻ በጳጳስ፣በቆሞስ፣በካቴክስትና በቁምስና ምዕመናን ምክር ቤት ልዩ ክትትል የሚደረገለት ጋብቻ ነው።

**``እግዚአብሔር ታላቅ ነገርን አደረገልን፥ ደስም አለን " \መዝ.125፡ 3) በማለት ምዕመናን ምስጋና አቅርበዋል።**

በሐረር ሀገረ ስብከት በጋብቻ ምክንያት ከቅዱስ ቁርባን ከ10-32 ዓመታት ርቀው የነበሩ በትዳር ሕይወት ውስጥ ያሉ የቁምስናችን አባላት በሕገ ቀኖና መሠረት የእያንዳንዱ ቤተሰብ ሕይወት በጥልቀት ተፈትሾ የብፁዕነታቸውን ይሁንታ አግኝቶ ከጸደቀ በኋላ ካቶሊካውያን ወገኖች ልዩ ዝግጅት ሲያደርጉ ቆይተው የተክሊል ትምህርት፣ ሱባኤና ንስሐ በአግባቡ ከፈጸሙ በኋላ የቅልቅል ጋብቻ( Mixed Marriage) በቤተክርስቲያን ጋብቻ መዝገብ ላይ ቀኖና ህግ በሚፈቅደው መሠረት ካህን ባለበት የፊርማ ሥነ ሥርዓት ተደርጎ ሰኔ 9 ቀን 2016 ዓ.ም 11 ቤተሰቦች ሥጋ ወደሙን ለመቁረብ በቅተዋል። ይህንን ታላቅ ነገር ለነዚህ ቤተሰቦች በዚሁ በፋሲካ ወራት በማድረጉ በሐረር ካቶሊካዊ ሰበካ ታላቅ ደስታ ሆኗል። ለዚህ መርሃ ግብር መሳካት ላለፉት 2 ዓመታት ቀንና ሌሊት ሲለፉ የቆዩ ክቡር ቆሞስ አባ ታዴዎስ ግዛውና ምእመናን ምክር ቤት ምስጋና በማቅረብ ለጉዳዩ ትኩረት ተሰጥተው ከህገ ቀኖና አንጻር በጥልቀት የመረመሩ ክቡር አባ ራሞን ዲያዝ (የጂግጂጋ ቅዱስ ዮሴፍ ቆሞስና የሃገረስብከቱ ጋብቻ ጉዳይ ሊቅ) እና ጥምረቱን ያጸደቁልን ብጹዕ አባታችን አቡነ አንጀሎ ፓጋኖ (የሐረር ሃገረ ስብከት ጳጳስ)፣ ሱባኤ ያስገቡልን ክብርት ሲ/ር ደስታ እግዚአብሔር እድሜና ጤና ይስጣችሁ በማለት ምስጋና ቤተሰቦች አቅርበዋል። በመጨረሻ የዚህ እድል ተጠቃሚ የሆናችሁ ምእመናን እግዚአብሔር ይህንን ታላቅ ነገር ስላደረገላችሁ ለእኛም በረከት ስላስገናችሁልን እናመሰናለን።

*ስንታየሁ ሲሳይ/ድሬ-ዳዋ, ኢትዮጵያ*

**ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ከኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የሕፃናት እንክብካቤ እና ጥበቃ ቢሮ ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው**

**ከቶ ከአፋችሁ ክፉ ቃል አይውጣ፤ ነገር ግን ለሚሰሙት ደስ የሚያሰኝና ለማነጽ የሚጠቅም ለሰዎችም አስፈላጊ የሆነውን ቃል ተናገሩ" (ኤፌ. 4:29)**



በክቡር ካቲኪስት ወርቁ ጦጤ
ከኮንሶላታ ማርያም ቤተ ጸሎት

# “የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ” (ኤፌ 4፡30)

*ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች የተቀበሉትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ እንዳያሳዝኑ እንዲህ እያላቸው በወንድማዊነት ምክር ይመክራቸል። “ለምትዋጁበት ቀን ማረጋገጫ እንዲሆናችሁ የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ” (ኤፌ. 4፡30)።*

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች በፍቅር የምላቸው እናንተ ከዓለም ተለይታችሁ እግዚአብሔር ለእራሱ ሥራ የተመረጣችሁ እና ቅዱሳን የእግዚአብሔር ልጆች እንድትሆኑ ዓለም ሳይፈጠር በክርስቶስ አማካይነት የተመረጣችሁ ናችሁ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በተጨማሪም ለኤፌሶን ሰዎች የሚላቸው። በስሙ መመረጣችሁ ብቻ ሳይሆን፤ በቤቱ ለአልገሎት መልካም ዜና የሆነውን የእውነት ቃል በሰማችሁ ጊዜ በክርስቶስ አምናችኋል፤ እንዲሁም እርሱ ሊሰጣችሁ ተስፋ ባደረገላችሁ በመንፈስ ቅዱስ ታትማችኋል። ይህ መንፈስ ለክብሩ ምሥጋና እንዲሆን እግዚአብሔር የራሱ የሆኑትን በሙሉ እስኪዋጅ ድረስ ልናገኝ ላለው ርስታችን መያዣችን ነው። እያላቸው ነው። (ኤፌ. 1፡13-14)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ “ይህ መንፈስ ለክብሩ መሥጋና እንዲሆን አግዚአብሔር የራሱ የሆኑትን በሙሉ እስኪዋጅ ድረስ ልናገኝ ላለው ዕርስታችን መያዣችን ነው” ማለቱ ምን ማለቱ ነው? ይህን ጥያቄ ልብ ብለን ልናስተውል ይገባናል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ሁላችንንም ወደ አባቱ ሊወስደን በክብር ይመጣል። ዳግመ ሲመጣ ደግሞ ስለ መንግሥተ ሰማይ ሊያስተምረን አይደለም የሚመጣው። እርሱ ወደ አብ (ወደ አባቱ) ከመሄዱ በፊት ለኤፌሶን ሰዎች (አማኞች) የተሰጣቸው የቤት ሥራ አለ። ይህን የቤት ሥራን በእምነትና በእውት ለሠሩት ሰዋች በሙሉ ሽልማት ሊሰጣቸው ነው። ይህም ሽልማት እገኡብጠር በክርስቶስ አማካይነት ያዘጋጀልን “መንግሥተ ሰማይ ነው።” ይህ ርስታችሁ የሆነው መንግሥተ ሰማይ እንድትወርሱ የሚያበቃችሁ ብርታትንና ጥንካሬ፤ በሚሰጣችሁ “በመንፈስ ቅዱስ ታትማችኋል” (ኤፌ 2፡13) እያላቸው ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌስን አማኞች አደራ ነው እያላቸው ያለው ይኸውም፡- ነገ በክርስቶስ አማካይነት ለምትወርሷት ሀገር (መንግሥተ ሰማይ) የሚያበቃችሁን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑት፤ እራሱን ካሳዘናችሁ የእናንተ ሕይወት ሕልውና አደጋ ላይ ነው፤ ስለዚህ “አታሎ ወደ ኃጢአት በሚመራ ምኞት የተበላሸውን አስቀድሞ ትኖሩበት የነበረውን፤ አሮጌውን የተፈጥሮ ባሕርይ አስወግዱ። አእምሮአችሁም በመንፈስ ይቀደስ። በእውነተኛ ጽድቅና ቅድስና በእግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰውነት ልበሱ። ስለዚህ ውሸት አትናገሩ፤ ሁላችንም የአንድ አካል ክፍሎች ስለሆንን እርስ በርሳችን እውነት እንናገር። ተቆጡ በቁጣችሁ ግን ኃጢአት አትሥሩ ቁጣችሁም ሳይወገድ ፀሐይ አይጥለቅባችሁ። ለዲያብሎስም መግቢያ ቀዳዳ አትስጡት። ይሰርቅ የነበረው ከእንግዲህ ወዲያ አይስረቅ፤ ይልቅስ ለችግረኞች ይሰጥ ዘንድ ገንዘብ እንዲኖረው በገዛ እጆቹ መልካም ነገርን ይሥራ። ከቶ ከአፋችሁ ክፉ ቃል አይውጣ፤ ነገር ግን ለሚሰሙት ደስ የሚያሰኝና ለማነጽ የሚጠቅም ለሰዎችም አስፈላጊ የሆነውን ቃል ተናገሩ” (ኤፌ. 4፡22-29)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን በሙሉ አናንተን ወደ እግዚአብሔር አያቀረባችሁም እግዚአብሔር ለመረጣችሁ ዓላማ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ለእግዚአብሔር ተለይታችሁ እራሱን በሚያመሰግን ሕይወት በፊቱ ተመላለሱ። እናንተ በክርስቶስ አማካይነት መመረጣችሁ ለምድራዊ ሕይወት ሳይሆን፤ በምድር የክርስቶስ አምባሳደር ሆናችሁ፤ የመንግሥተ ሰማይ ዜጐች ሆናችሁ የምሥራቹን የወንጌል ቃል በእምነትና በእውነት መስክሩ እያላቸው ነው። ምስክርነታችሁ ደግሞ በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርና በእውነት ይሁን። እናንተ ለእውነትና ለእውነት እንድትኖሩ፤ በመንፈስ ቅዱስ ታርማችኋል። ይህ የታተማችሁበት መንፈስ ቅዱስ ለምትዋጁበት ቀን ማረጋገጫ ይሆናችኋል እያላቸው ነው።

ስለዚህ መራራነት፣ ንዴት ቁጣ፣ ሁከት፣ ስድብና ማናቻውም ዓይነት ክፋት ሁሉ ከእናንተ ወዲያ ይራቅ። ይልቅስ እርስ በርሳችሁ ደጐችና አዛኞች ቸሮችና ርህሩሆች ሁኑ። እግዚአብሔር በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተም እርስ በርሳችሁ ይቅር ተባባሉ። (ኤፌ. 4፡ 31-32)።

ትላንት እግዚአብሔር በቅዱስ ጳውሎስ አማካይነት በኤፌሶን ሰዎች (አማኞች) የተናገረው ዛሬም እግዚአብሔር በመንፈሱ ሆኖ ለእኔም፣ ለአንተም፣ ለአንቺም፣ ለእርስዎም እየተናገረን ነው። ይኸውም “ሰዎች የተዋጁበት ቀን ማረጋገጫ እንዲሆናችሁ የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ” (ኤፌ. 4፡30) እያለን ነው።

እናታችን ቤተክርስቲያን ለእኛ ለልጆቿ በሚስጢረ ሜሮን አማካይነት አስተምራን ሰባት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ሰጥታናለች ይኸውም፡- 1. ጥበብ 2. ልቦና ወይም ማስተዋል 3. ምክር 4. ኃይል (ጽናት) 5. ዕውቀት 6. አምልኮ (እምነት) 7. እግዚአብሔርን መፍራት ናቸው።

እናታችን ቤተክርስቲያን ይህንን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ስትሰጠን እኛ በተሰጠን ስጦታዎች በእምነትና በእውነት ተጠቅመንበት በሕይወታችን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎችን እንድናፈራበት ከእኛ ከልጆቿ ትጠብቃለች። ይኸውም፡- የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች 1. ፍቅር 2. ደስታ 3. ሰላም 4. ትእግስት 5. ቸርነት 6. በጐነት 7. ሊጋስነት 8. ጨዋነት 9. እምነት 10. ትሕትና 11. ራስን መግዛት እና 12. ንጽህና ናቸው።

መንፈስ ቅዱስ በእናታችን በቤተክርስቲያን አማካይነት ቅዱሳን ስጦታውን ሰጥቶናል። ነገር ግን ስንቶቻችን ነን በስጦታው በእውነት ተጠቅመን አሥራ ሁለቱን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎችን በሕይወታችን ያፈራነው ይህ ጥያቄ ለሁላችን ነውና፤ በሕሊናችን ልናስተውል ያስፈልገናል።

እናታችን ቤተክርስቲያን እኛ እውነተኛ የክርስቶስ ተከታዮች እድንሆነ ሚስጢረ ሜሮን አስተምራን ሰባቱን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ሰጥታናለች፤ እኛም አምነን “አሜን” ብለን በእምነት ተቀብለናል። ነገር ግን መቀበላችን ብቻ የሕይወታችን ዋስትና አይደለም። እናታችን ቤተክርስቲያን ሰባቱን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ስትሰጠን፤ እኛ በተሰጠን ስጦታ ተጠቅመን ስሟን እንድናስከብራት ነው። ዛሬ እናታችን ቤተክርስቲያን በሰጠችን መጠን፤ ከእኛ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎችን በሕይወታችን አፍረተን በሰዎች ሁሉ የተትረፈረፈ ውብ ፍሬዎችን ለማየት ትፈልጋች። ነገር ግን የመንፈስ ቅ'ዱስ ዎች ዛሬ በእኛ መካከል ጐልቶ እየታየ ነው ወይ? በእውት በተሰጠን በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ፍሬዎች ሆነናል ወይ? በእኛ በራስ ወዳድነት ቅዱስን የእግዚአብሔርን መንፈስ አላሳዘንም ወይ? በእውነት እግዚአብሔር በመንፈሱ የእያንዳንደችንን ሕሊና እየወቀሰን ነው።

ሁሉም ምእመን የምስጢረ ሜሮን ትምህርት ተምሮ ሰባቱን የመንፈስ ቅዱስን ስጦታዎች ተቀብሏል። ነገር ግን መቀበላችን ብቻ ምን ጥቅም አለው? እኔ ተቀብዬ ነበር፤ ማለታችን እኛን የክርስቶስ ተከታዮች አያስብለንም። ዛሬ እናታችን ቤተክርስቲያን በሚስጢረ ሜሮን አማካይነት አስትምራን የሰጠችን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በእኛ በራስ ወዳድነት እንዳይዳፈኑ ስጋት ነው። ስለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ አማኞች እንዲህ የሚላቸው፡- “የመንፈስ ቅዱስን ሥራ አታዳፍኑ” (1ተሰ. 5፡19)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም “መንፈስ ቅዱስን አትቃወሙት” (ሐሥ. 7፡51)እያለን ነው። መንፈስ ቅዱስ ዛሬ ስጦታውን ለእኛ ሲሰጠን በሕይወታችን ተጠቅመን እውነተኛ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎችን እንድናፈራ እና ለነገ ለነፍሳችን ስንቅ የሚሆነንን መተማመኛችንን በከንቱ እንዳንጥልና እርሱን እንዳናሳዝነው ይፈልጋል። ምክንያቱም አንዳንድ የተሰጡን ስጦታዎች በእኛ በሟች ሥጋችን ፍላጐት ከውስጣችን ጠፍቶ መንፈሳውያን መሆናችን ቀርቶ አለማውያን ሆነን እርስ በርሳችን ስንታመስ እንገኛለን።

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በመልእክቱ እንዲህ ይለናል “በእናንተ መካከል ያለው ጦርነትና ጠብ ከየት የመጣ ነው? ከሰውነታችሁ ውሰጥ ከሚዋጋው ከሥጋዊ ምኞታችሁ አይደለምን? አንድን ነገር ለማግኘት ትመኛላችሁ፣ ግን አታገኙም፤ ስለዚህ ሰውን ትገድላላችሁ” (ያዕ. 4፡ 1-2)።

“እግዚአብሔር በውስጣችሁ ያሳደረው መንፈስ ለእርሱ ብቻ እንደሆነ በብርቱ ይመኛል ያለው በከንቱ ነውን?” (ያዕ. 4፡5)።

ስለዚህ የተወደዳችሁ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ሆይ ትናንት የተቀበልነው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በእያንዳንዳችን ልብ አለና ዛሬም ጊዜውም አልረፈደምና ወደ እራሳችን እንመለስና በልባችን ውስጥ ያለውን የመንፈስ ቅዱስ እሳትን እናቀጣጥለው። መንፈስ ቅዱስ ዛሬም ቢሆን እሳቱን ለማንቀሳቀስ ለሚፈልገው ሁሉ ሥራውን ለመሥራት ይፈልጋልና ልባችንን ለመንፈስ ቅዱስ ክፍት እናደርግለት።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ትላንትና ለፊፌሶን አማኞች “ለምትዋጁበት ቀን ማረጋገጫ እንዲሆናችሁ፤ የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ”(ኤፌ 4፡ 30)። እንዳላቸው ሁሉ እኛም ዛሬ ለመላው ካቶሊካውያን አደራ የምላችሁ፡- “ትናንት በሚስጢረ ሜሮን አማካይነት የተቀበላችሁትን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን በከንቱ አታሥቀሩ።

ብዬ እለምናቸዋለሁኝ። ደግሞም “የመንፈስ ቅዱስን ሥራ አታዳፍኑ” ይልቁንም በቁጭት በፍቅር ሥራ አቀጣጥሉት። እግዚአብሔር በትላንቱ አይወቅሰንም በዛሬ ሕይወታችን እንድንኖርበት ይፈልግል።

በመጨረሻ ላይ ሐዋርያው ቅድስ ጳውሎስ ለሮሜ አማኞች በመሐሪው በእግዚአብሔር ስም እንደለመናቸው ሁሉ፤ እኔም በዚህ መንፈስ ሆኜ ሁላችሁንም “እንግዲህ ወንድሞቼ ሆይ እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ ሕያውና የተቀደሰ መሥዋዕት አድርጋችሁ ሁለንተናችሁን እንድታቀርቡ በመሐሪው በእግዚአብሔር ስም እለምናችኋለሁ፤ ይህም ማቅረብ የሚገባችሁ ቅንነት ያለው እውነተኛ የእግዚአብሔር አገልግሎት ነው። መልካሙንና ደስ የሚያሰኘውን ፍጹም የሆነውንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ እንድትችሉ አእምሮአችሁን በማደስ ሕይወታችሁ ይለወጥ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉት”፡፣ (ሮሜ. 12፡ 1-2) እያልኳችሁ እለምናችኋለሁ።

ስለዚህ እናታችን ቤተክርስቲይን ባስትማረችን በሚስጢረ ሜሮን አማካይነት በተቀበልናቸው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን በዚህ ባለንበት ዘመን እንዴት አድረግን መጠቀም እንዳለብን ትላንተ እግዚአብሔር በሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አማካይነት ለኤፌሶን አማኞች እንደመከራቸው፤ ዛሬም እግዚአብሔር በመንፈሱ ሆኖ እኔንንም፣ አንተንም፣ አንቺንም እና እርሶንንም እንዲህ እያለነ እየመከረን ነው፡- “እንግዲህ እንዴት እንደምትኖሩ በጥንቃቄ አስተውሉ እንደ ጥበበኞች እንጂ እንደ ሞኞች አትኑሩ። ይህ ዘመን ክፉ ስለሆነ በማናቸውም አጋጣሚ ጊዜ ተጠቀሙ። ስለዚህ የጌታ ፈቃድ ምን እንደሆነ አስታውሱ እንጂ ሞኞች አትሁኑ”። (ኤፌ. 5፡ 15-17) ቃሉን በማስተዋል አንብቡት።

እንግዲህ ከትላንትናው ከስንፍና ሕይወታችን ወደ ብርቱ መንፈሳዊ ሕይወት ሆነን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ያስፈልገናል። ቃሉ እንደሚለን “ስለዚህ ከከፉ ሕሊና እነዳን ነጻ ልባችንን ተረጭተን፤ ሰውነታችንንም በንጹሕ ውና ታጥበን ቅን ልብና እውነተኛ እምነት ይዘን ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ” (ዕብ. 10፡22)።

ማጠቃለያ በአነበብነው በሰማነው በእግዚአብሔር ቃል መሰማት ብቻ ሳይሆነ፤ በሰማነው ባነበብነው በእግዚአብሔር ቃለ በእውነት ኖረን እናታችን ቤተክርስቲይን አስተምራን በሰጠችን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን መጠቀምና ፍሬዎችን በሕይወታችን ማፍራት እንድንችል መንፈስ ቅዱስ ጸጋውን በሕይወታችን ዘወትር ያብዛልን። እግዚአብሔር አባታችን ለሀገራችን ፍጹም ሰላሙን ይስጠን። መንፈስ ቅዱስ ለሀገራችን መሪዎችም ሆነ ለዓለም መሪዎችም የጥበብንና የማስተዋልን የልቦና ጸጋውን ያብዛላቸው አሜን።

የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ” (ኤፌ 4፡30)

LINK

No. 267 July 2024 P. O. Box 2454 Tel. (0111) 55 03 00 Addis Ababa

You are most welcome to
Subscribe and
Advertise on LINK

## Ethiopian Catholic Bishops Embark on Ad Limina Visit to Rome

The Ethiopian Catholic Bishops Conference went to the Holy See in Rome for their quinquennial Ad Limina visit with Pope Francis. This pilgrimage allows the Bishops to renew their bonds with the Holy Father, visit the tombs of Saints, explore Vatican Dicastery, and share updates on the Ethiopian Catholic Church, including both its triumphs and its struggles.

The Ad Limina visit commenced on June 22, 2024, with two days of retreat and reflection. The Ad Limina visit continues with a series of meetings with Vatican Dicasteries. These meetings aim to align the Ethiopian Church's thinking with that of the Holy See and Pope Francis.

As part of their visit, the Bishops visited the Pontifical Ethiopian College in Vatican, an institution with over a century of history. They met with college officials and students, fostering a sense of community and connection.

The Ad Limina visit was concluded on June 28, 2024, with a celebration of Mass at Saint Peter's Basilica. Following the Mass, the Bishops hold an extended meeting with the Pope to discuss fundamental Church matters. With Pope Francis's guidance and support, the Ad Limina visit served to strengthen the Ethiopian Church's dedication to its mission.

This Ad Limina visit holds particular significance as it marks the return of His Excellency Abune Tesfaselasie, Bishop of Eparchy of Adigrat, who was unable to attend previous Bishops gatherings for the past four years due to the ongoing conflict in Ethiopia.

While the Ad Limina visit typically occurs every five years, this gathering was postponed due to the COVID-19 pandemic. As a result, this marks the first Ad Limina visit for Ethiopian Bishops in ten years in the presence of all Ethiopian Bishops united in prayer for peace in the Church and the Nation.

## The Ethiopian Catholic Church Welcomes New Bishop for Vicariate of Nekemte

The Holy Father has appointed the Reverend Fr. Getahun Fanta Shikune, C.M., until now spiritual director of the Lazarist School of Addis Ababa and spiritual director of the Daughters of Charity in Ethiopia, as vicar apostolic of Nekemte, Ethiopia on 16 July 2024.

Fr. Getahun Fanta Shikune, C.M., was born on 25 February 1973 in Aleku Sassi, West Wollega, in the apostolic vicariate of Nekemte. He was awarded a master's degree in human resources from DePaul University, Chicago, United States of America.

He entered the seminary of the Congregation of the Mission and studied at Saint Francis Capuchin Institute of Philosophy and Theology in Addis Ababa. He was ordained a priest on 1 July 2001.

Fr. Getahun Served as parish priest at Holy Saviour, Sako, and Saint Mary, Metcha. Led the major seminary of his Institute and served two terms (2010-2013 & 2013-2016) as superior of the Province of Ethiopia for the Congregation of the Mission. Currently, he is the director of the Lazarist School of Addis Ababa and spiritual director of the Daughters of Charity of Ethiopia.

This appointment marks the third bishop named by the Holy See in 2024, joining Bishop Lukas of Emdibir and Bishop Dejene of Soddo. The Ethiopian Catholic Bishops Conference expresses heartfelt congratulations on the appointment of Fr. Getahun Fanta.


## Ethiopian Catholic Church Adigrat Diocese Staff Visit Headquarters

On June 21, 2016, Adigrat Diocese leadership and staffs met with representatives from the Ethiopian Catholic Church Bishops' Conference General Secretariat for an experience -sharing workshop.

The purpose of the visit, as explained by Ato Alem, Head of Programs for the Adigrat Diocese's Social Development Department, was to reflect on the challenges faced over the past four years and to strengthen and encourage the Diocese. The visit also focused on exploring options to improve the diocese's organizational structure, financial and human resource management, and technology-based support.

Ato Bekele Moges, Head of Social Development for the Ethiopian Catholic Church Bishops' Conference General Secretariat, welcomed the Adigrat delegation and opened the experience-sharing workshop by introducing the General Secretariat staff from the presented department. The General Secretariat staff presented an overview of the Ethiopian Catholic Church's ten-year plan and the progress made, ongoing, and planned for each work area in Programs, operations, finance, HRM and Information technology.

The workshop concluded with a question-and-answer session and the establishment of future directions.




## The Episcopal ordination of Reverend Father Dejene Hidoto Gamo, OFM Cap, has been announced for September 15, 2024, at Holy Trinity Catholic Cathedral in Soddo

Father Dejene, the newly appointed shepherd for the Vicariate of Soddo, succeeds Bishop Tsegaye, whose resignation prompted the appointment of Bishop Seyoum of Hosanna as interim leader. Father Dejene's selection ensured a seamless transition and continued strong leadership for the Catholic Church in Soddo.

His Eminence Cardinal Berhaneyesus, Metropolitan Archbishop of Addis Ababa and President of the Catholic Bishops' Conference of Ethiopia, will serve as the Consecrator for the Episcopal ordination. His Excellency Abune Seyoum and His Excellency Abune Angelo Pagano will join as co-consecrators. The ordination is expected to be a grand gathering of the Catholic community, with the attendance of all Bishops, Priests, Religious, and the faithful.

A Capuchin Franciscan priest born on March 21, 1972, Wolaita, Ethiopia, Father Dejene currently serves as the Pastoral Coordinator of the Vicariate of Soddo. His journey to priesthood began with education at Boditti Elementary and Junior Secondary School, followed by Boditti High School, and culminated in ordination in 2000 after completing Philosophical and Theological studies.

Father Dejene's service is marked by diverse roles, including parish priest, social welfare directorof the Capuchins, chaplain, guardian, and director of a technical and vocational training institute. His dedication to both spiritual and academic growth is evident in his achievements, which include earning a Bachelor of Arts in Sociology and Social Anthropology from Addis Ababa University and a Master of Arts in Public Ethics from St. Paul University in Ottawa, Canada. He further enriched his pastoral experience with a year in Quebec City, Canada.

Father Dejene's commitment to his faith and community is reflected in his ongoing service and leadership.

## Nuncio Expresses Gratitude for His Service in Ethiopia

Addis Ababa, July 18, 2024 – Archbishop Antoine Camilleri, the Apostolic Nuncio to Ethiopia, expressed heartfelt gratitude for his four years of service during a farewell Mass held at the Holy Savior Catholic Church.

In his address, Archbishop Camilleri commended the Ethiopian people for their warm hospitality and unwavering support. He highlighted his visits to all dioceses in the country and expressed profound respect for the work of the Catholic community. As he prepares to assume a new role in Cuba, the Nuncio requested the continued prayers of the Ethiopian people.

His Grace further added, “I would also like to thank the Ethiopian government and people and pray that God blesses Ethiopia.”

His Eminence Cardinal Berhaneyesus Souraphiel, the Metropolitan Archbishop of Addis Ababa and President of Catholic Bishops' Conference of Ethiopia, also expressed his sincere appreciation on behalf of the Ethiopian Catholic Church and the Catholic community of Ethiopia for His Grace's service to Ethiopia.

The Cardinal stated, “The presence of the Apostolic Nuncio in our country has been a great blessing, not only for us Catholics but for all Ethiopian Community.” He wished the Nuncio all the best in his new assignment.

The farewell Mass was organized by the Superior Generalate of the Ethiopian Catholic Religious Orders.

For if you forgive men their trespasses, your heavenly Father will also forgive you: But if ye forgive not men their. trespasses, neither will your Father forgive your trespasses. (Matthew 6:14-15)

# Training on Safeguarding of Children and Vulnerable Adults for AMECEA Church Leadership

The Association of Member Episcopal Conferences in Eastern Africa (AMECEA) secretariat hold a Training on Safeguarding for AMECEA Church Leadership that took place from 1st July to 4th July 2024 at Roussel House, Donum Dei, Karen in Nairobi.

It was an invitation to the Leadership of the Church to interact and give their advice on how best the document motu proprio ‹‹Vos Estis Lux Mundi›› can be expedited in the region.

‹‹Vos Estis Lux Mundi›› (You are the Light of the World) is an apostolic letter of Pope Francis that established new procedural norms to combat sexual abuse and ensure that bishops and religious superiors are held accountable for their actions. It establishes universal norms, which apply to the whole church.

The seminar explored the following topics in details: Exploring Protection: Concerns among Children and Vulnerable Adults; Responding to Abuse: a Pastoral Concern that includes commitments and resolutions. In this workshop Abba ABENET Abebe, C.M. who is the National Director for Family, Laity and Youth Ministry participated as a delegate for CBCE-GS.



# St. John Paul II Multi-Purpose Center Officially Inaugurated

St. John Paul II TVET
College & Youth Center

A new vocational training center named after St. John Paul II was officially inaugurated at the Ledeta Catholic Cathedral compound in Addis Ababa. The center aims to provide young people with various vocational skills to help them become self-sufficient and contribute to the country's development.

This center, located at the Ledeta Catholic Cathedral compound in Addis Ababa, was officially inaugurated and blessed on July 13, 2024, by His Eminence Cardinal Berhaneyesus Souraphiel, the Metropolitan Archbishop of Addis Ababa, President of the Catholic Bishops' Conference of Ethiopia. The ceremony was attended by religious leaders, government officials, community representatives, and other invited guests.

His Eminence Cardinal Berhaneyesus expressed his joy at witnessing the center's progress and thanked all those who had contributed to its establishment. His Eminence reiterated the Church's commitment to youth and emphasized the importance of vocational training in empowering young people to become self-sufficient and contribute to the country's growth.

Rev. Abba Petros Berga provided a comprehensive overview of the center, tracing its development from conception to its current state. He emphasized the significance of this vocational training center in addressing the needs of young people and highlighted the importance of collaborative efforts to make it a success. Following the introduction of the center's management team, Rev. Berga invited Dr. Ephrem Tekle, the driving force behind the entire project, to speak. He referred to Dr. Ephrem Tekle as the 'Academic Strategic Architect'.

Dr. Ephrem explained that the center will offer a variety of vocational training programs, including some that have not been previously available in the area. He announced that training in four different fields is set to begin soon and that the center plans to expand its offerings over time.

The guests invited expressed their enthusiasm for the center, emphasizing its potential to empower young people and contribute to the country's development. They commended the Church for its commitment to human development and holistic approach to serving the community.

Engineer Zekarias, Academic Dean of St. John Paul II TVET, announced that the center will provide training in music, computer science, video graphics, and building maintenance. With qualified instructors already on board, the center will soon open its doors to applicants. The Dean encouraged parishes to identify and nominate promising young individuals for these training programs.

In essence, the St. John Paul II Multi-Purpose Center represents a significant step forward in the Catholic Church's efforts to provide vocational training and empower young people in Ethiopia.

# ዲያቆን ወ/የሱስ መኔዶ ከዚህ ዓለም ድካም አረፉ

ዲያቆን ወ/የሱስ መኔዶ ከአባታቸዉ ከአቶ መኔዶ ሆይሶ እና ከእናታቸዉ ወ/ሮ ሱጋሜ እሎሬ በቀድሞ አጠራር በሸዋ ጠቅላይ ግዛት በከምባታ አውራጃ በጠምባሮ ወረዳ በአሞሾራ ቀበሌ በዛሬው አጠራር በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በሀዲያ ዞን ሌሞ ወረዳ በ1ኛ አሞሾራ ቀበሌ ልዩ ስሙ ግዳና ማርዱንቾ በሚባልበት መንደር በቀን 10/05/1933 ዓ.ም ተወለዱ።

ዲያቆን ወ/የሱስ በልጅነታቸው ቤተሰቦቻቸውን እያገዙ ከቆላ ወደ ደጋ እየተመላለሱ በእረኝነት ያገግሉ ነበር። በተወለዱበት አካባቢ የነበረውን የጣዖት አምልኮ ይጠየፉ ስለነበር ይህንንም ለማስቀረት ካደረባቸው ፍለጎት የተነሳ ፈጣሪ በሚያውቀው ጥበብ በወቅቱ የክርስትና ሃይማኖት ባልተስፋፈበት ስለ ክርስትና ሃይማኖት በሰሙት መረጃ በመነሳት ወደ ዋገበታ ቅዱስ መስቀል ካቶሊካዊት ት/ቤት የቀለም ትምህርት ለመማር በመወሰን ወላጆቻቸውን በማማከር በ1948 ዓ.ም ጎዞአቸውን ወደ ት/ቤት አመሩ።

ዲያቆን ወ/የሱስ ትምህርታቸውን ከ1ኛ-3ኛ ክፍል እየተማሩ ጎን ለጎን የካቶሊክ ሃይማኖት መሰረታዊ ትምህርት (ትምህርተ ክርስቶስ) በመማር በታህሳስ 29/1951 ዓ.ም ምስጢረ-ጥምቀት ተቀበሉ። ከዚያም የጌታችን



የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደምና ሥጋን ተቀብለዋል። ይህም ሙሉ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አባል የሆኑበትና በህይወታቸው ከፍተኛ ደስታ የተሰማበት መሆኑን ባልደረቦቻቸው አሁንም ይነገራሉ፡፤

ዲያቆን ወ/የሱስ መሥዋተ ቅዳሴ ለማስቀደስና ለማምለክ በየሳምንቱ እሁድ እሁድና በተለያዩ መንፈሳዊ በዓላት ጊዜ ለብቻቸውም ቢሆን ፀሐይና ብርድ ሳይበግራቸዉ ከቤታቸው እስከ ዋሳራ ቅድስት ቲሬዛና የጃጁራ ቅዱስ ጴጥሮስና ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያናትን ሳይሰለቹ ይመላለሱ ነበር።

ዲያቆን ወ/የሱስ ለወንጌል ባላቸው ጥማትና ፍላጎት የተነሳ ይህንን ቤተ ክርስቲያን ወደ ተወለዱበት አከባቢ ማለትም ወደ ሳዳማ ለማምጣት እና ሕዝቡ ወደ ወንጌል አቅጣጫ እንዲመለሱ ለማድረግ እንዲመቻችላቸው ጓደኞችን እና ፍላጎት ያላቸውን መመልመል ግድ ሆነባቸው። በዚሁ መሰረት ካቴክስት ዮሐንስ ለዕመንጎን፣ ካቴክስት ገብረ ወልድ ሱላሞን፣ ካቴክስት ገብረ ፃድቅ ጀካሞን፣ አቶ ገ/ማርያም ወቴን፣ አቶ ገ/ሚካኤል መኔዶን፣ ካቴክስት ኃ/የሱስ ዶሊሶንና ሌሎችንም በማስተማር የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታዮችና ጠንካራ ምዕመናን እንዲሆኑ ያደረጉ የእምነት አባት ነበሩ።

ዲያቆን ወ/የሱስ በተወለዱበት አከባቢ ስለ ወንጌል የሚያስተምሩ እና የሚመሰክሩ ወጣቶችን ስላፈሩ አቋርጣው የነበሩ ትምህርታቸውን ለመቀጠል በ1952 ዓ.ም ወደ ዋሳራ ቅድስት ቲሬዛ ካቶሊክ ትምህርት ቤት በመሄድ ከ4ኛ እስከ 6ኛ ክፍል ተከታትለው በ1954 ዓ.ም 6ኛ ክፍል አጠናቀዋል። በተጨማሪ ከቀለም ትምህርት ጎን ለጎን የምስራች ወንጌል ትምህርት ከፈራንሳይ ሀገር ከመጡ ከሚስዮናዊ አባ ስልቬስትር ተምረዋል።

ዲያቆን ወ/የሱስ ከ1955 ዓ.ም በአመቾ ዋቶ፣ በበርኩንቾ፣ በበሌሳ፣ በሆሳዕናና በሌሎችም በወቅቱ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ት/ቤት ለተከታታይ 3 ዓመታት ከመንፈሳዊ ትምህርት ጎን ለጎን በመምህርነት አገልግለዋል። በመቀጠልም በተወለዱበት በሰዳማ አካባቢ ይህ የቀለም ትምህርት በወንጌል መስፋፋት ጎን ለጎን እንዲጀመር አባ ስልቬስትሪን በ1954 ዓ.ም ጥያቄ አቀረቡ። ይህም ጥያቄ አባ ሰልቬስትሪ ከመመለሳቸዉ በፊት ስለ ሰዳማ መረጃ ሲጠይቁ በወቅቱ የነበሩ የሥርዓቱ ደጋፊዎች ስለ አከባቢ መልካም ከመነገር ይልቅ መጥፎ መረጃ በመስጠት ለጊዜው ፈቃድ እንዳይሰጥ አድርጎ ነበር።

በመጨረሻም ዲያቆን ወ/የሱስ በተለያዩ ጊዜ በጥያቄ ሲያስቸግሩ አባ ሳልቬስትሪ እስከ አከባቢ መጥተው እንዲያዩና እንዲጎበኙ አመቻቹ።ይህም ትምህርትቤቱ በግዳና ማርዱንቾ ወይም በዱና ማርዱንቾ ቢሆን ይመረጣል የሚል ተስፋ ተሰጣቸው። በዕለቱ በጣም እንደተደሰቱ ባልደረቦቻቸዉ አሁንም ይነገራሉ። በሌላ በኩል በወቅቱ የስርዓቱ ደጋፊዎች የነበሩ ፈረንጆች ሀዲያን ዘመናዉ ትምህርት ካስተማረ ህዝቡ ለእኛ አይታዘዝም በማለት ተስፋ እንዲቆርጡ አድርጎ ነበር።በመጨረሻም ዲያቆን ወ/የሱስ ተስፋ ካለመቁረጥ ወደ ባህል ዳኛ ኤርጎጎ መሎሬ ጋር በመሄድ መረጃ ያደርሳሉ፤ በመቀጠልም ከዳኛው ጋር የተለያዩ አማራጭ መንገድ በመፈለግ በታችኛው ሰዳማ ትምሕርት ቤት የሚሰራበት ቦታ አገኙ። ከዚያም ወደ አባ ሰልቬስተሪ ጋር በመሄድና እሳቸውን ይዞ በመምጣት በ1955 ዓ.ም በታችኛው ሰዳማ ትምህርት እንዲጀመር አደረጉ።

ዲያቆን ወ/የሱስ ከቀለም ትምህርት ጎን ለጎን የጀመሩትን የምስራች ወንጌል የማወቅ ጥማት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመምጣቱ የእሳቸውና ጓደኞቹ ስለ ወንጌል ጥልቅ እውቀት ለማግኘት ከቀድሞ ሆሳዕና ሀገረ ስብከት ጳጳስ ከብፁዕ አቡነ ወልደጊዮርጊስ ተምረዋል።

ዲያቆን ወ/የሱስ በ1958 ዓ.ም ለአንድ ዓመት በሆሳዕና ሚስዮን ከነ ቤተሰባቸው ተቀይረው ሙሉ ካቴክስት በመሆን ሰዳማ፤ ሌንችቾ እና አምቢቾ እየተመላለሱ ሰርተዋል።

ወደ ገፅ 15 ዞሯል

This page is sponsored by CRS

“According to your faith [your trust and confidence in My power and My ability to heal] it will be done to you.” (matthew 9 29)

# ወ/ሮ ምህረት ገብረልዑል ከዚህ ዓለም ድካም አረፉ

**1945-2016**

*" የጌታ ፈቃድ ይሁን ብለን ዝም አልን"*
*(ሐዋ. 21፥14)*



ወ/ሮ ምህረት ከአባታቸው መምህር ገብረልዑል ውለድ ጽይዮን ከአናታቸው ወ/ሮ ፈቃዱ መሐሪ የካቲት 14 ቀን 1945 ዓ.ም. በአስመራ ከተማ ተወለዱ። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በአስመራ ከተማ ሲያጠናቅቁ ፤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታችውን መቀሌ በሚገኘው አፄ ዮሐንስ ት/ቤት አጠናቀዋል። ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በቅድስት ማርያም ካቶሊክ ልጃገረዶች ት/ቤት በአካውንቲንግ እና በአጻደ ሕጻናት መምህርነት ሙያ በዲፕሎማ ተመርቀዋል። በሥራ ዓለም በእርዳታ ማቋቋሚያና ማስተባበሪያ ኮሚሽን ፣ በኢትዮጵያ ካቶሊክ ጽ/ቤት፤ በተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮምሽን(UNHCR) ፤ በሂሳብ አያያዝ ሰርተዋል።

ወ/ሮ ምህረት 1973 ዓ.ም. በመቀሌ በሚገኘው ልደተማርያም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከአቶ ኢሳያስ ተክኤ ሥርዓተ ተክሊል ፈጽመዋል። በትዳር ሕይወት ዘመናቸው ከባለቤታቸው ጋር በታማኝነት በመኖር ሁለት ወንድና ሶስት ሴት ልጆች ፤ አራት የልጅ ልጅ አፍርተዋል።

ወ/ሮ ምህረት በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ከልጅነታቸው ጀምሮ የቤተ ክርስቲያን አፍቃሪያ ወዳጅ ሲሆኑ ባላቸው አቅም ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ከፍ ብላ እንድትታይ የሚችሉትን ሁሉ ያደርጉ እናት ነበሩ። ከእነዚህ ጥቂቶቹ በየቀኑ አራቱን የመቁጠሪያ ምስጠራት ጸሎት ከቅዳሴ በኋላ በግልና በጋራ በመጸለይ ጸሎት በመምራት ለብዙዎች በተግባራችው ወንጌልን የሰበኩ የጸሎት ሰው ነበሩ ። በቅዱስ ሚካኤል ፣ በኪዳነ ምህረት፣ በቅዱስ አንጦንዮስ እና በተለያዩ ማህበር በመሳተፍ ክርስቲያናዊ አገልግሎት ሰጠዋል። ወ/ሮ ምህረት በሕሙማንን በመጠየቅ የታወቁ ሲሆን የአልጋ ቁራኛ ሆነው ቤት ለቀሩ ምዕመናን ካህን በመያዝ በራሳችው ትራንስፖርት በቤታችው ድረስ በመሄድ መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲያገኙ ድርሻቸውን የተወጡ እናት ነበሩ። እንደዚሁም በገጠር ለሚገኙ ቤተ ክርስቲያናት ሕብስት፣ ወይን ፣ ነዋየ ቅዱሳን አልባሳት በመለገስ ይታውቃሉ። በቁምስናቸው ልደተማርያም ቤተክርስቲያን ዘመናቸውን ሁሉ ሳያቋርጡ በግንባር የሚያስቀድሱ፣ ለቁምስናዋ በግንባር የቆሙ እናት ነብሩ።

ወ/ሮ ምህረት ባደረባችው ሕመም በሕክምና ሲረዱ ቆይተው ሰኔ 12 ቀን 2016 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም ድካም ወደ አምላካቸው ሲሄዱ፣ አስክሬናችው በቅዱስ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ካቶሊክ መካነ መቃብር አርፏል። የሚወዷት የሚያፈቅሯት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የአገልግሎት ዋጋቸውን ታስጥልን። ነፍሳቸው በአብርሃም፣ በይስሃቅ፣ በያዕቆብ አጠገብ ቸሩ እግዚአብሔር አምላካችን ያኑርልን። ለቤተሰባቸውና ለልጆቻችው ለወዳጆቻቸው ሁሉ መጽናናትን ይስጥልን።

---

**ዲያቆን ወ/የሱስ ...**

ከገፅ 14 የዞረ

ከዚያም የሰዳማ ክርስቲያኖች ወደ ሰዳማ ተመልሰዉ እንዲያስተምሩ በጠየቁት መሰረት በ1959 ዓ.ም ወደ ተወለዱበት አከባቢ እንደተመለሱ የሥራ ባልደረቦቻቸው ይናገራሉ።

ዲያቆን ወ/የሱስ በ1955 ዓ.ም ከወ/ሮ ትሬዛ አቦሴ በካቶሊክ ቤ/ክርስቲያን ሥርዓት ምስጢረ ተክሊል ፈጽመዋል። ከባለቤታቸው ጋር በመሆን ሙሉ ተግባር ወደ የምስራች ወንጌል ማስፋፋት አገልግሎት ላይ ተሰማሩ። የሰደማ ቅድስት ሃና ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አባለት በሁሉም አቅጣጫ እየሰፉ በመሄዱ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ የሆነ ካህን እንዲመደብ በወቅቱ ለነበሩ የሶዶ ሆሳዕና አገረ ስብከት ጳጳስን ማለትም ብፁዕ አባታችን ዶሚንኮ ማርኔዝ በመጠየቅ ሙሉ ቁምስና እንዲሆን በጠየቁት መሰረት የሰደማ ቅድስት ሃና ቤተክርስቲያን ቁምስና እንዲሆን ያስደረጉ ጠንካራ የእምነት አባት ነበሩ።

ዲያቆን ወ/የሱስ በቅድስት ሃና ቤተ ክርስቲያን የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ከመሆናቸውም በፊት ቤተ ክርስቲያኑና ትምሕርት ቤቱ ያለበት የመሬት ስፋት በጣም አነስተኛ እና ለሕዝበ ክርስቲያኑና ለተማሪዎቹ አማካይ ቦታ ካለመሆኑ የተነሳ ሌላ አማራጭ ቦታ መፈለግ ግድ ሆነባቸው። ለዚህም በወቅቱ ከነበሩት ክርስቲያኖች ጋር በመሆን ለመንግስት ጥያቄ በማቅረብ በተለይም በደርግ ሥርዓት አጀማመር ወቅት የጠምባሮ ወረዳ የገበሬዎች ዋና ሊቀ መንበርና የባህል ዳኛ የነበሩትን አበጋዝ ጋዶሬ ዲጀጎን አማከሩ። ለዚህም እንዲመቻቸዉ የአከባቢ ሽማግሌዎችንና ተዋቂ ግለሰቦችን ጥያቄ እንዲያቀርቡ በማነሳሰት አሁን የቅድስት ሃና ቤተ ክርስቲያን እና የቅድስት ሃና 1ኛ ደረጃ ትምሕርት ቤት ያለበትን ቦታ በ1968 ዓ/ም እንዲገኝ አስችሏሉ። ለዚህም የእሳቸው ሚና በጣም ትልቅ የነበረ ጠንከራ የሕዝብ አባት ነበሩ።

ዲያቆን ወ/የሱስ አዲሱን ለቤተ ክርስቲያን በተሰጠው ቦታ ቤተ ክርስቲያንና የካቴክስቶች ማሰልጠኛ ትምሕርት ቤት እንዲሰራና በተጨማሪም ትምሕርት ቤት እንዲሰራ በተሰጠው ቦታ ትምሕርትቤትን እንዲያሰሩ በወቅቱ ለነበሩ ለሶዶ ሆሳዕና ሀገረ ስብከት ጳጳስ ለነበሩ ለብፁ አባታችን ለዶሚኒኮ ማርኖዝ ጥያቄ በማቅረብ ግንባታዉ በ1969 ዓ/ም ተጀምሮ በ1970 ዓ/ም እንዲጠናቀቅ ያደረጉ የሃይማኖት አርበኛ አባት ነበሩ።

ዲያቆን ወ/የሱስ በሶዶ ሆሳዕና ሀገረ ስብከት ካሳዩት ከመንፈሳዊ እድገትና ካላቸው ተስጥኦ የተነሳ ሶዶ ሆሳዕና ሀገረ ስብከት ክርስቲያኖችን በመወከል በ1960 ዓ. ም. በተደረገው 2ኛ የቫቲካን ዓለም አቀፍ ክርስቲያኖች ጉባዔ ተሳተፊ የነበሩ ጠንከራ የወንጌል አርበኛ አባት ነበሩ።

ዲያቆን ወ/የሱስ በ1977 ዓ/ም በሀገራችን ኢትዮጵያ በተከሰተው ረሃብ ምክንያት የአከባቢ ማህበረሰብ እንዳይጎዳ በማለት ከአባ ቶማስ ቢሌዝ አማካይነት ለሶዶ ሆሳዕና ሀገረ ስብከት ጳጳስ ለነበሩት ለብፁዕ አባታችን ለዶሚኒይኮ ማርኖዝ የእርዳታ ጥያቄ አቀረቡ። ይህም በወቅቱ ምላሽ በማግኘት ሕዝቡ በአደጋ እንዳይጎዳ የእህል፣ ሕክምና ቁሳቁሶች እና አገልግሎት በስፋትና በጥራት እንዲሰራ ያደረጉና ለዚሁም ተግባር ከአከባቢ ጠንከራ ወጣቶችን ማለትም ወ/ትንሳኤ ገዕኖሬ፣ ተስፋዬ ቀልብሶ፤ ማርቆስ ላዕላጎ፣ ካቴክስት ወልዳ መስቀል እርጎጎ፣ ካቴክስት ሰለሞን ዶለኖ እና ሌሎችንም ወጣቶችንም በማስተባበር የሰሩና የመልካም ተግባር ምሳሌ አባት ነበሩ።

ዲያቆን ወ/የሱስ በክርስትና ሕይወታቸውና በመንፈሳዊነት እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስ እውቀትና ጥበብ በሚያስምሩት በአገላለፅ ችሎታቸዉ ሁሉም አካላት ይደነቁና ይማረኩ ነበር። ለዚህም በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ባለትዳር ዲያቆን እንዲሆን ለብፁዕ አባታችን ዶሜኒኮ ማርኖዝ ሀሳብ የወቅቱ የቅድስት ሃና ቤተ ክርስቲያን ቆሞስ የነበሩ አባ ቶማስ ቢሌዝ ሀሳብ በማቅረብና ሀሳቡም ለብፁዕ አባታችን ዶሙኒይኮ ማርኖዝ ዘንድ ተቀባይነት አገኘ። ከዚያም ለኢትዮጵያ ጳጳሳት ጉባዔ አጀንዳ ቀርቦ ከተወያዩ ቦኋላ በብፁዕ ካርዲናል ጳውሎስ አማካይነት ለሮም ሊቀ ጳጳስ ለነበሩ ለብፁዕ አባታችን ለዳግማዊ ዮሐንስ ጳውሎስ ጥያቄ ቀርቦ ጥያቄውም በእሳቸው መልካም ፈቃድ አገኘ። በዚሁ ሁኔታ በ1980 ዓ. ም. በኢትዮጵያ ደረጃ የመጀመሪያ ባለትዳር ቋሚ ዲያቆን ሆነው በድቁና ማዕረግ የተሾሙና በድቁንናቸው ለግማሽ ምዕተ ዓመት ቤተ ክርስቲያንን ያገለገሉ ድንቅ አባት ነበሩ።

ዲያቆን ወ/የሱስ

- በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ምዕመናን ሐዋርያዊ ምክር ቤት ምክትል ሰብሳቢ ሆኖ የሰሩ
- በሆሳዕና ሀገረ ስብከት ለ50 ዓመታት የሰደማ ካቴክስትች ማሰልጠኛ ዋና ዳይሬክተር
- በሀዋሳ ሀገረ ስብከት ዳንጉራ የካቴክስቶች ማሰልጠኛ መምህር
- በመቂ ሀገረ ስብከት ጂጌሳ ካቴክስት ማሰልጠኛ መምህር
- በሶዶ ሀገረ ስብከት ዱቦ ካቴክስት ማሰልጠኛ መምህር በመሆን ያገለገሉ ድንቅ መሪ ነበሩ።

ዲያቆን ወ/የሱስ ከተለያዩ የሥራ ባልደረቦች ጋር በመሆን በሶዶ ሆሳዕና ሀገረ ስብከት ሁሉንም ቤተ ክርስቲያን በአካል በመሄድ አገልግለዋል። በተላይም ሆሳዕና ለክህነት መዘጋጃ ትምህርት ቤት የሸለላ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በከፍተኛ ደረጃ በመንቀሳቀስ የምስራችዶሙኒይኮ ወንጌል ጥልቅ ትምህርት ያስተማሩ የእውቀት አባት ነበሩ።

ዲያቆን ወ/የሱስ በአከባቢ በተለያዩ በልማት ሥራዎች ሕዝቡ እንዳይጎዳ ቤተ ክርስቲያኒቱ በማስተባበር የመንገድ የጤና፤ የዉሃ፤ የትምህርትና የመብራት አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ብዙ ጥረት ያደርጉ አባት ነበሩ። በተጨማሪም ካላቸው ከሕዝብ ፍቅርና ከወንጌል አስተምህሮ የተነሳ በተለያዩ ጊዜ በሀገር እና ከሀገር ዉጭ በመጓዝ በተለያዩ ቦታዎች የወንጌልን አገልግሎት በተለይም በጣሊያን አገር በእስራኤል አገር ቅዱስ ቦታዎችን ጉብኘት አድርገዋል። በሌላ በኩል በደቡብ አፍሪካ በሌሴቶ በስዊዝላንድ የወንጌል አገልግሎት የሰጡ የወንጌል አርበኛ ነበሩ። ከዚህም ሌላ በሄዱበት ሀገራት ሁሉ ያለውን መንፈሳዊና ቁሳዊ ቅርሶችን ማለትም ሕንድ ውቅያኖስን፣ እትላንቲክ ውቅኖስን፣ የ12ቱ ሐዋርያት መታሰቢያ ሙዚየምን፣ የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ታጋይ የነበሩ ኔሊሳን ማንዴላ የታሰሩበትና ሌሎችንም ታሪካዊ ቦታዎችን የመጐብኘት ዕድል አግኝተዋል

ዲያቆን ወ/የሱስ በህይወት ዘመናቸው ያደረጉትና ለሕዝቡ ያሳዩት ፍሬዎችን በጥቂቱ ስንመለከት የብዙ ቋንቋ ማለትም ሀዲይሳ፤ ካምባትሳ፤ አማርኛ፤ እንግሊዝኛ አቃለጥፈው ስለሚናገሩ ለብዙ ሰዎች የትርጉም ሥራዎችን ይረዱ ነበር። በሌላ በኩል በካቶሊክ ቤተክርስቲያን በሀዲይሳ ለሚነገሩት ለመስዋዕተ ቅዳሴ እና የተለያዩ የፀሎት መጽሀፍቶችን በሀዲይሳ በመተርጎም አሻራቸዉን አኑራዋል። በተጨማሪ ህትመት የተደረገ እና ያልተደረጉ የተለያዩ መጽሀፍቶችን የደረሱ አባት ነበሩ።

ዲያቆን ወልደየሱስ ካበረከቱአቸው መንፈሳዊና ማህበራዊ አገልግሎቶች

- ሕዝቡን ከጨለማ ወደ ብርሃን እንዲሻገሩ መሪ በመሆን
- በዘመናዊ ትምሕርት ማህበረሰብ በተለያዩ ሙያዎች ማለትም በቀለም ትምህርት እና በመንፈሳዊ ትምህርት ሥልጠና እንዲያገኙ በማገዝና በማስተማር
- በመንፈሰዊ ትምህርት ይሁን በቀለም ትምህርት የቀድሞ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስተር የነበረ ክቡር ሀይለማርያም ደሳለኝን ጨምሮ በተለያዩ ሙያዎች መስከ የተሰማሩ ክርስቲያኖችን፤ ካቴክስቶችን፤ ሲስተሮችን፤ ካህናትን፤ ጠንከራ የሥራ ባህል እንዲኖራቸው እና በስነ ምግባር የታነፁ እንዲሆኑ ያደረጉ አባት የነበሩ
- በቅድስት ሃና ቤተክርስቲያን ሰደማ ከ100 በላይ ደናግላንና ካህናትን ለስብከተ ወንጌል አገልግሎት ያዘጋጁ እንዲወጡ የበኩላቸውን ድርሻ የተወጡ አባት ነበሩ።

ዲያቆን ወ/የሱስ የተቸገሩትን የሚረዱ፤ የታረዙትን የሚያለብሱ፤ የተረቡትን የሚያበሉ፤ የሰውና የፈጣሪ ፍቅር ያላቸው፤ በወንጌል የኖሩ፤ ከአንደበታቸው ክፋት የማይናገሩ፡ ሰው አክባሪ፤ ትሁት፤ ቸር፤ ለጋስ፤ ሥራ ወዳድ፤ የተጣለውን የሚያስተርቁ የፍቅር ሰው ነበሩ።

ዲያቆን ወ/የሱስ ባለትዳርና የ5 ወንድና የ6 ሴት ልጆች ከእነዚህም 3ቱ የካቶሊክ ደናግል ሲሆኑ የልጅ ልጆቻቻዉ ደግሞ 15 ሆኖ በአጠቃላይ የ26 ልጆችን አይተዋል።

ዲያቆን ወ/የሱስ መኔዶ ባደረባቸው ህመም ምክንያት በተለያዩ የህክምና ማዕከላት ሲታከሙ ቆይተዉ ሰኔ 29 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 12 ሰዓት በተወለዱበት 83 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። ስርዓተ ቀብራቸዉም በሰዳማ ቅድስት ሃና ቤተክርስቲያን መካነ መቃብር በቀን ሀምሌ 1 ቀን 2016 ዓ.ም. ወዳጅ ዘመዶቻቸው፤ የሥራ ባልደረቦቻቸው በተገኙበት ተፈፀመ።

ነፍሳቸውን ፈጣሪ በአፀዳ ገነት ያኑርልን እያልን ለቤተሰቦቻቸዉ፤ ለወዳጅ ዘመዶቻቸው ለቅድስት ሃና ሰደማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ምዕመናን ለሆሳዕና ሀገረ ስብከት ምዕመናንና ለጓዳኞቻቸው እንዲሁም ለኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር መጽናናትን እንዲሰጥ እንመኛለን።

*ሐምሌ 1/2016 ዓ/ም*

This page is sponsored by CAFOD/SCIAF/TROCAIRE

" God is faithful, who has called you into fellowship with his Son, Jesus Christ our Lord.". (1 Cor. 1:9)

# LINK

## የሕክምና ተልዕኮ እህቶች ማኅበር
## Medical Mission Sisters

*Called to be a healing presence at the heart of a wounded world*

**“ብርሃናችሁ በዓለም ሁሉ ይብራ”** ማቴ. 5: 16

**“let your light shine”** Mt. 5 - 16



ማህበራችን እ.ኤ.አ በ1925 በሲስተር አና ደንግል (ዶር) Sister Anna Dengel (Dr.) በአሜሪካ ተመሠረተ

**የማህበራችን ዋነኛው ዓላማ -** የክርስቶስን የማዳን ሥራ አገልግሎት በሕክምናና በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ።

**መስፈርታችን -**

- በቅድሚያ ሕይወቷን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አገልግሎትና ለድሆች መስጠት የምትፈልግ
- ለጸሎትና ለእግዚአብሔር ትልቅ ስፍራ ያላት
- በዓለም አቀፍ ማኅበር መኖርና ማገልገል የምትፈልግ
- የትምህርት ደረጃ 10+2 እና ከዚያም በላይ

ቦሌ ጌስት ሃውስ አካባቢ
ቤት ቁጥር - 68
አድራሻችን አዲስ አበባ / ቂርቆስ - ወርዳ 01

የስልክ ቁጥር 0911055968 / 0911400139 / 0911106561 / 0923241466

ፖ.ሣ. ቁጥር 2891

| | |
|---|---|
| አድራሻችን | ወልቂጤ ጉራጌ |
| ስልክ ቁጥር | 011 3 30 52 37 |
| ፖ.ሣ. ቁጥር | ሲስተር ንግሥት ብሩ 11 |

## በአዲስ አበባ ካቶሊክ ሃገረስብከት ሴቶች ዕድገት ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ማዕከል

(ካሀሴዕማ/ቴ/ሙ/ት/ስ) አ.አ.

**Catholic Archdiocese Women's Promotion Technical and Vocational Education & Training Center**

(CAWPC / TVET) A. A

**“ Come and see us. You will be most welcome! WE ARE WAITING FOR YOU! ”**

በዝቅተኛ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ የሚገኙና የቀለም ትምህርታቸውን በተለያዩ ምክንያቶች አቋርጠው የሙያ ስልጠና ፍላጎት ያላቸውን ወጣቶች ለማገዝ በአነስተኛ ክፍያ የስልጠና አገልግሎት በማግኘት ለሥራ ብቁ የሚያደርጉና ለገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴ የሚያዘጋጁ የሙያ ስልጠናዎችን በመስጠት ላይ እንገኛለን።

**በአጫጭር ስልጠና (Short training)**
በደረጃ አንድና በደረጃ ሁለት
Level (1) one and Level (2) two

**የሚሰጡ ስልጠናዎች**

1 ልብስ ቅድና ስፌት
2 ህትመትና ማቅለም
3 የተሻሻለ የሽመና ሥራ
4 ጥልፍ በእጅና በስፌት መኪና
5 ሹራብ በእጅና በማሽን
6 ምግብ ዝግጅትና መስተንግዶ

ሀ - ከ 3-6 ወራት አጭር ኮርስና
ለ - ለ 10 ወራት በመረጡት ሙያ ሰልጥነው እራስዎን ለሥራ ያዘጋጁ።

**በማዕከአችን የስልጠና አገልግሎቱ ቀጣይነት በጥራት የሚያመርታቸውን የዕደጥበብ ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ በመግዛት ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንጋብዛልን።**

**አድራሻችን**
አራዳ ክ/ከ ፒያሳ
ካቶሊክ ካቴደራል ት/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ

**ስልክ ቁጥር**
011 111 4786 / 011 157 5927

**E-mail**
cawpc@ethionet.et

**ስለ“ፍቅርና ሰላም ጋዜጣ” አስተያየት ካለዎት በስልክ ቁ. (0111) 55 03 00 በመደወል ለፍቅርና ሰላም ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ያካፍሉን!**



## የኮንሰላታ ማርያም ልውካን እህቶች እና አባቶች ገዳም

“የኮንሰላታ የአጽናኝቷ ማርያም ልውካን እህቶች እና አባቶች ገዳም ዓለም አቀፍ ተልዕኮ ያለው ሲሆን የገዳማችን ልዩ ምልክት እግዚአብሔር ኢየሱስን አጽናኝ አድርጎ ለዓለም እንደሰጠ እኛም ለዓለም ሁሉ የምሥራቹን ቃል ማብሰር ነው።”


**“.... ሕዝቤን አጽናኑ አጽናኑ” (ኢሳ. 40 :1)**

እኛ የአጽናኝቷ ማርያም ልውካን እህቶች እና አባቶች በብፁዕ ዮሴፍ አላማኖ አማካኝነት ቶሪኖ በሚባል በጣሊያን ከተማ ገዳማችን ተመሰረተ።

የተጠራነውም በፍቅር እንድንኖርና በተጠራንበት የፍቅር ሕይወት የእግዚአብሔርን ቃል ላልሰሙት ለማብሰር ነው። ይህንንም የምናደርገው በሕብረት በመኖር፣ ዛሬ በምንገኝባቸው አገሮች፣ በአፍሪቃ፣ በእስያ፣ በአውሮፓ፣ በሰሜንና በደቡብ አሜሪካ ከማህበረሰቡ ጋር በመኖር የተለያየ አገልግሎት በመስጠት ላይ እንገኛለን።

**የገዳማችንን መንፈስ ለመከተልም ሆነ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ፍቅር እና መፅናናት ላልደረሳቸው ለማድረስ ለምትሹ እህቶች/ ወንድሞች ሁሉ -** የገዳማችን መጠይቅ እንደሚከተለው ነው

1 በቅድሚያ ራሷን/ራሱን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አገልግሎት መስጠት የምትፈልግ/ የሚፈልግ
2 የእግዚአብሔርን ቃል ላልደረሳቸው ማብሰርና የተልኮ ሕይወት ለመኖር ሙሉ ፍላጎት ያላት/ ያለው
3 10+3 ወይም ዲፕሎማ 12+3 Degree (ዲግሪ) ከዛም በላይ በማንኛውም ዘርፍ የትምህርት ማስረጃ ያላት/ ያለው
4 ለአባቶች 12ኛ ክፍል ይቀበላሉ



Our Lady of Consolata
Pray for Us

**“ታላቅነቴን በሕዝቦች መካከል ያውጃሉ” (ኢሳ. 66 :18)**

ስልክ
0912-14-26-37
011-3-21-01-47 / 48

የፖ.ሳ ቁጥር
145069 / 22748

አድራሻ
ኮንሰላታ ሲስተሮች/ አባቶች አዲስ አበባ መካኒሳ ከመካነየሱስ ሴሚናሪ ፊት ለፊት

## በላይ ተክሉ ብስኩት ቤት
*Belay Teklu Pastry*

- ለሰርግ
- ለልደት
- ለተለያዩ ግብዣዎች

**የሚሆኑ ኬኮችን አዘጋጅቶ ይጠብቃችኋል**





አድራሻችን
ልደታ መልሶ ማልማት ፓርክ ፊት ለፊት
አዲስ አበባ

የመ.ሣ.ቁ 1928

0911203273
0911208810
0913303412

## የካቶሊክ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ መጻሕፍት መደብር
**Catholic Church Book Shop**

ፒያሳ - ካቴድራል ት/ቤት ገባ ብሎ በስተቀኝ

ፖ. ሣ. ቁ. 2454 አዲስ አበባ

ስልክ: (0111) 55 03 00



**ወንጌልን በጋራ እንስበክ**

**ሌሎች ቢያነቡዋቸው ትምህርት ያገኙባቸዋል ብለው የሚያምኑባቸውን መጣጥፎች እና የወንጌል አስትምህሮዎች ይላኩልን**

ፖ. ሣ. ቁ. 2454 አዲስ አበባ | ስልክ - (0111) 55 03 00 | ፋክስ (0111) 55 31 13 | E-Mail - scpr@eccsdco.org